Ethiopian Railways Corporation

ERC LABOR ASSOCIATION

የኢምባኮ መሠረታዊ የሠራተኞች ማህበር

# የኢትዮጲያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን

# እና

# የኢትዮጲያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን መሰረታዊ የሰራተኞች ማህበር

# የሕብረት ስምምነት

**650/2013**

ጥር 2011

## ማውጫ


መግቢያ ..... 1

አንቀጽ 1 ..... 1

አጭር ርእስ ..... 1

አንቀጽ 2 ..... 1

ትርጉም ..... 1

አንቀጽ 3 ..... 4

የሕብረት ስምምነት ዓላማ ..... 4

አንቀጽ 4 ..... 6

ለሠራተኛ ማህበር ዕውቅና ስለመስጠት ..... 6

አንቀጽ 5 ..... 6

የሕብረት ስምምነቱ የተፈፃሚነት ወሰን ..... 6

አንቀጽ 6 ..... 6

የኮርፖሬሽኑ መብቶች ..... 6
የኮርፖሬሽኑ ግዴታዎች ..... 7
የሠራተኛ መብቶች ..... 11
የሠራተኛ ግዴታዎች ..... 11
የማህበር መብቶች ..... 13
የማህበር ግዴታዎች ..... 14
የጋራ ውይይትና ግንኙነት ..... 15
ልዩ/አስቸኳይ ስብሰባ ..... 15

አንቀጽ 7 ..... 16

የቋሚ ሠራተኛ ቅጥርና የሙከራ ጊዜ ..... 16

አንቀጽ 8 ..... 17

መደበኛ የሥራ ሰዓት እና የሳምንት ዕረፍት ጊዜ ..... 17

አንቀጽ 9 ..... 18

የትርፍ ሰዓት ሥራ ..... 18

አንቀጽ 10 ..... 18

ደመወዝ መክፈያ ቀን እና ስለ ደመወዝ አከፋፈል ..... 18
አንቀጽ 11 ..... 19
የሥራ አፈፃፀም ግምገማና ዓላማ ..... 19
የሥራ ውጤት መመዘኛ ዓላማ ..... 19
የሥራ ውጤት መመዘኛ ቅጽ ይዘትና አሞላል ..... 19
የምዘና ወቅት ..... 20
የሠራተኛ የሥራ ውጤት መግለጫ ከላይ እንደተገለፀው ከተሞላ በኋላ ..... 20
የሥራ አፈፃፀም ምዘና ውጤት አሞላል ስርዓት ..... 21
አንቀጽ 12 ..... 22
የደመወዝ ጭማሪ እና ማበረታቻ ..... 22
አንቀጽ 13 ..... 22
የአየር ፀባይ አበል ..... 22
አንቀጽ 14 ..... 23
የጉዞ (የውሎ) አበል ተመንና አከፋፈል ..... 23
አንቀጽ 15 ..... 24
ቅጥር፣ ዕድገት፣ ምደባ እና ውክልና ..... 24
አጠቃላይ ሁኔታ ..... 24
ዕድገት ..... 24
ስለ ደረጃ ዕድገት ኮሚቴ መቋቋም ..... 25
የመረጃ አቀራረብና የምርጫ ውጤት ..... 25
የዕድገት መወዳደሪያ ነጥቦች ..... 25
ቅጥር ..... 26
ተጠባባቂ ምደባ እና ውክልና መስጠት ..... 26
አንቀጽ 16 ..... 26
ዝውውር ..... 26
ጊዜያዊ ዝውውር፣ ..... 27
ቋሚ ዝውውር፣ ..... 27
በኮርፖሬሽኑ በኩል ..... 27
በሠራተኞች በኩል ..... 27
አንቀጽ 17 ..... 29
የዓመት ፈቃድ ..... 29

የህመም ፈቃድ ... 30
የወሊድ ፈቃድ ... 31
የአባትነት ፈቃድ ... 32
ሕጋዊ ግዳጅ ለማስፈፀም የሚሰጥ ፈቃድ ... 32
የጋብቻ ፈቃድ ... 33
የሀዘን ፈቃድ እና ተጨማሪ ድጋፎች ... 33
አንቀጽ 18 ... 34
የሥራ ሰዓት ዕረፍት ... 34
አንቀጽ 19 ... 34
የሕዝብ በዓላት ... 34
አንቀጽ 20 ... 34
ትምህርትና ሥልጠና ... 34
አንቀጽ 21 ... 36
በሥራ ላይ ስለሚደርስ አደጋ ... 36
አንቀጽ 22 ... 36
ከሥራ ጋር ግንኙነት ለሌላቸው ህመሞች የሚደረግ የሕክምና ወጪ ... 36
አንቀጽ 23 ... 37
የደንብ ልብሶችና የመከላከያ መጠቀሚያዎች ... 37
አንቀጽ 24 ... 39
መዝናኛና ስፖርት ... 39
አንቀጽ 25 ... 39
የሳጥን(ካዝና) መጠበቂያ ክፍያ ... 39
አንቀጽ 26 ... 40
የሥራ ውል መቋረጥ፣ የሥራ ስንብትና የካሣ ክፍያ ... 40
አንቀጽ 27 ... 41
አስተዳደራዊ የሥነ-ሥርዓት እርምጃዎች ... 41
የሥነ ሥርዓት እርምጃ አወሳሰድ መርህ ... 41
የሥነ ሥርዓት እርምጃ ዓላማ ... 41
የሥነ ስርዓት እርምጃ አፈፃፀም ... 42

ቀላል እና ከባድ የሥነ ሥርዓት ጥሰቶች የሚያስከትሉት ቅጣት ..... 43
ቅጣት በግል ማህደር የሚቆይበት ጊዜ ..... 43
አንቀጽ 28 ..... 43
በአገልግሎት የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ..... 43
አንቀጽ 29 ..... 43
የቅሬታ አቀራረብ ስነ ስረዓትና አወሳሰን ..... 43
አንቀጽ 30 ..... 44
ምክክር ..... 44
አንቀጽ 31 ..... 45
የመጓጓዣ አገልግሎት ስለመስጠት ..... 45
አንቀጽ 32 ..... 45
ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅም ክፍያ ..... 45
አንቀጽ 33 ..... 46
የሌሊት አበል ..... 46
አንቀጽ 34 ..... 49
የሥራ አስተባባሪዎች አበል ..... 49
አንቀጽ 35 ..... 49
የጽዳት መጠበቂያ ..... 49
አንቀጽ 36 ..... 50
የወተት አበል ..... 50
አንቀጽ 37 ..... 50
ስምምነቱ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ ..... 50
አንቀጽ 38 ..... 51
የሕብረት ስምምነት ስለማሻሻል ..... 51
አንቀጽ 39 ..... 51
ስምምነት ስለመፈራረም ..... 51
አባሪ 1: የሥነ ሥርዓት እርምጃ አወሳሰድ ሠንጠረዥ ..... 52

አባሪ 2: የደንብ ልበሶችና የመከላከያ መጠቀሚያዎች የሚፈቀድላቸውን የሥራ መደቦች ዝርዝር ሠንጠረዥ ................................ 75

አባሪ 3: የፈረቃ አበል የሚከፈላቸው የሥራ መደቦች ሠንጠረዥ ........................................................ 84

አባሪ 4: የሥራ አስተባባሪዎች የሥራ መደቦች ዝርዝርና የደረጃ ሠንጠረዥ ........................................ 90

አባሪ 5: የልዩ ሙያ አበል ተከፋዮች ሰንጠረዥ ................................................................................... 91

## መግቢያ

በኮርፖሬሽኑ ውስጥ ምቹ የስራ አካባቢን በመፍጠር የሠራተኛን ውጤታማነት ለማሳደግ በሠራተኛውና በኮርፖሬሽኑ መካከል የሚደረግ የህብረት ስምምነት ጉልህ ድርሻ ይኖረዋል፡፡ ሠራተኞች በመልካም ሥነ-ምግባርና በሙሉ ሙያዊ አቅም ከፍተኛ የህዝብና የመንግስት ኃላፊነት የተጣለበትን ኮርፖሬሽን ለማገልገል መብትና ግዴታቸውን በግልፅ ማስቀመጡ እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡የባቡር ኢንዱስትሪ የሚጠይቀውን ጠንካራና ከፍተኛ ሙያዊ ሥነ-መግባር የተላበሰ ሠራተኛ በመፍጠር ዘርፉን በሀገር አቀፍና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ በማድረግ ሃገራችን ከዘርፉ ልታገኝ የሚገባትን ሁለንተናዊ ጥቅም ማረጋገጥ ይቻል ዘንድ በኮርፖሬሽኑና በሰራተኞች መካከል የሚደረግ የህብረት ስምምነት የራሱን አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡መብቱና ጥቅሙ ተከብሮለት ኃላፊነቶቹንና ግዴታውን የሚወጣ፣ የስራ አፈፃፀሙ በውጤት የሚለካ፣ለኮርፖሬሽኑ ተልዕኮ መሳካት ቅድሚያ የሚሰጥ፣ ለተቋሙ ደንበኞችና በለድርሻዎች ደህንነት ተገቢውን ጥንቃቄ የሚያደርግ፣ አውቀቱንና ሙያውን በማዘመን ለኮርፖሬሽኑ ውጤታማነት ቀን ከለሊት የሚተጋ ሰራተኛን መፍጠር የባቡር ዘርፉ የሃገሪቱን ኢኮኖሚ በታለመው መልኩ እንዲደግፍ ለማድረግ በህብርት ስምምነት የሚቀመጡ ዝርዝር የአሰሪና የሰራተኞች መብትና ኃላፊነቶች ወሳኝ በመሆናቸው ይህን ህብረት ስምምነት መፈራረም አስፈልጓል፡፡ በመሆኑም፡-

ይህ የሕብረት ስምምነት በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት በተቋቋመውና በሚተዳደረው ከዚህ በታች "ኮርፖሬሽን" እየተባለ በሚጠራው በኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን

እና

በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 እና 494/98 (እንደተሻሻለው) መሠረት በተቋቋመውና በተመዘገበው ከዚህ በታች "ማህበር" እየተባለ በሚጠራው የኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን መሠረታዊ ሠራተኛ ማህበር መካከል በሚከተሉት ዝርዝር ሁኔታዎች ላይ ዛሬ ጥር ___2011 ዓ.ም ተፈርሟል፡፡

### አንቀጽ 1
### አጭር ርእስ

ይህ የሕብረት ስምምነት "2ተኛው የሕብረት ስምምነት" ተብሎ በአጭሩ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 2
### ትርጉም

በዚህ ሕብረት ስምምነት ውስጥ የሆኑ አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር

2.1 **"ኮርፖሬሽን"** ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 141/2000 መሠረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን ማለት ነው፡

2.2 **"አሠሪ"** ማለት አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሰዎችን በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 እና 494/98 አንቀጽ 2 በተመለከተው መሠረት ቀጥሮ የሚያሰራ ኮርፖሬሽን ነው፡

2.3 **"ሠራተኛ"** ማለት በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 እና 494/98 አንቀጽ 4 መሠረት ከአሠሪው ጋር በቅጥር ላይ የተመሠረተ የሥራ ግንኙነት ያለው ግለሰብ ነው፡፡ ሆኖም በኮርፖሬሽኑ መመሪያ መሠረት የሥራ መሪዎችና የሥራ ኃላፊዎች ተብለው የተገለፁትን አይጨምርም፡

2.4 **"ማህበር"** ማለት የኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን መሠረታዊ የሠራተኞች ማህበር ማለት ነው፡

2.5 **"ቋሚ ሠራተኛ"** ማለት በዚህ የሕብረት ስምምነት መሠረት የሙከራ ጊዜውን የጨረሰ እና ላልተወሰነ ጊዜ ወይም ላልተወሰነ ሥራ የተቀጠረ የኮርፖሬሽኑ ቋሚ ቅጥር ሠራተኛ ማለት ነው፡

2.6 **"ጊዜያዊ ሠራተኛ"** ማለት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 10 መሠረት በኮርፖሬሽኑ ውስጥ ተቀጥሮ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ለተወሰነ ሥራ አገልግሎት የሚሰጥ ሠራተኛ ማለት ነው፡

2.7 **"የሕብረት ስምምነት"** ማለት የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 እና በማሻሻያ 494/98 መሠረት በኮርፖሬሽኑ እና በሠራተኛ ማህበር ወኪሎች መካከል ስለ ስራ ሁኔታዎች፣ ለሠራተኛ ስለሚገቡ ልዩ ልዩ ጥቅሞች፣ ስለ ሥራ ማበረታቻዎች፣ ስለ ሠራተኛውና ስለ ኮርፖሬሽኑ መብትና ግዴታዎች በጽሁፍ የተደረገ የስምምነት ሰነድ ነው፡

2.8 **"ደመወዝ"** ማለት አንድ ሠራተኛ ለሚያከናውነው ሥራ በየወሩ የሚከፈለው ወርሃዊ መደበኛ ክፍያ ሲሆን የጥቅማጥቅም ክፍያዎችን አይጨምርም፡

2.9 **"ቅድሚያ ደመወዝ"** ማለት ለሠራተኛው የሚሰጥ የደመወዝ ብድር ሆኖ በተወሰደው ወር ውስጥ ተመላሽ የሚሆን የቅድሚያ ክፍያ ማለት ነው፡

2.10 **"የውሎ አበል"** ማለት ሠራተኛው በኮርፖሬሽኑ ሥራና በሌሎች በኮርፖሬሽኑ አማካይነት ለሚመጡ ሥራዎች በቋሚነት ከተመደበበት የሥራ ቦታ ውጭ ሲላክ የሚከፈል አበል ነው፡

2.11 **"የአየር ፀባይ አበል"** ማለት ሠራተኛ የተመደበበት የሥራ ቦታ የአየሩ ፀባይ አስቸጋሪ በመሆኑ ምክንያት እንደ አየሩ ፀባይ በመንግስት አዋጅ መሠረት እየታሰበ የሚከፈል አበል ነው፡

2.12 **"ፈቃድ"** ማለት አንድ ሠራተኛ በመደበኛ የሥራ ሰዓት ከተመደበበት ሥራ ቀሪ ለመሆን የሚያስችለው ከደመወዝ ጋር ወይም ያለ ደመወዝ የሚሰጥ ፈቃድ ነው፡

2.13 **"ቅሬታ"** ማለት ሠራተኛው የሥራ ውል ወይም የሥራ ሁኔታ ሊነሳ የሚችል ወይም ከሌሎች የአስተዳደር ደንቦች አተረጓጎም ወይም አፈፃፀም የሚመነጭና በኮርፖሬሽኑና በሠራተኛ ማህበሩ ወይም በሠራተኛው ሊነሳ የሚችል አለመግባባት ነው፡

2.14 **"የሥነ ሥርዓት (የዲሲፕሊን) እርምጃ"** ማለት አንድ ሠራተኛ በዚህ የሕብረት ስምምነትና በአዋጅ 377/96 እና በኮርፖሬሽኑ በሚሰራባቸው መመሪያዎች ውስጥ የተመለከቱትን የሥነ-ሥርዓት ሕጎች በመተላለፍ ለሚደርሰው ጥፋት የሚወሰድበት የእርምት እርምጃ ነው፡

2.15 **"ዕድገት"** ማለት አንድ ሠራተኛ ከነበረበት የሥራ ደረጃ እና ደመወዝ ወደ ሌላ ከፍተኛ የሥራ ደረጃ እና ደመወዝ ላይ መመደብ ማለት ነው፡

2.16 **"ዝውውር"** ማለት ከአንድ የሥራ አካባቢ ወደ ሌላ የሥራ አካባቢ ወይም ከአንድ የሥራ መደብ ወደ ተመሣሣይ የሥራ መደብ በያዙት ደመወዝ እና የሥራ ደረጃ የሚፈፀም ጊዜያዊ ወይም ቋሚ ዝውውር ነው፡፡

2.17 **"ከሥራ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው አደጋ ወይም ህመም"** ማለት በሥራ ላይ ወይም ከሥራ ጋር ግንኙነት ባለው ምክንያት በተመደቡበት የሥራ ቦታ ባልታሰበ ሁኔታ ድንገት የሚደርስ አደጋ ወይም ከሥራው ጋር ግንኙነት ያለው በሐኪም የተረጋገጠ ህመም ነው፡

2.18 **"የቃል ማስጠንቀቂያ"** ማለት ለአንድ ሠራተኛ የቅርብ ኃላፊው ወይም የበላይ ኃላፊው የጥፋቱን ዓይነትና አድራጎት ሠራተኛው የጣሳቸውን የሕብረት ስምምነት አንቀፆች ጠቅሶ ከጥፋቱ እንዲታረምና እንዳይደግም በቃል የሚሠጠው ተግሳፅ ነው፡፡

2.19 **"የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ"** ማለት ሠራተኛው የፈፀመውን ጥፋት ፍሬ ነገር እና የተላለፈውን የሕብረት ስምምነት አንቀፅ ተጠቅሶ ለሠራተኛው የሚሠጠው ደብዳቤ ነው፡፡

2.20 **"የገንዘብ መቀጮ"** ማለት በዚህ ስምምነት የተዘረዘሩትን ጥፋቶች ሠራተኛው በመፈፀሙ ምክንያት ከደመወዙ ተቆራጭ የሚሆን የገንዘብ ቅጣት ነው፡፡

2.21 **"ከሥራ ማገድ"** ማለት በዚህ ሕብረት ስምምነት በተደነገገው መሠረት አንድ ሠራተኛ በፈፀመው ጥፋት ደመወዝ የማይከፈልበት ለተከታታይ 22 የሥራ ቀናት ከሥራ የሚታገድበት ነው፡፡

2.22 **"ከሥራ ማሰናበት"** ማለት አንድ ሠራተኛ ከባድ ጥፋቶች ተብለው ከተጠቀሱት እና ከሥራ ሊያሰናብት የሚችለውን ጥፋት አንዱን ፈጽሞ ሲገኝ ወይም ቀላል ጥፋቶችን በተደጋጋሚ ሲፈፅምና በሥነ ሥርዓት (ዲሲፕሊን) ኮሚቴ ተጣርቶ ጥፋቱ ሲረጋገጥ ከኮርፖሬሽኑ ጋር የነበረው ውል የሚቋረጥበት ሁኔታ ነው፡፡

2.23 **"ከደረጃ ዝቅ ማድረግ"** ማለት አንድ ሠራተኛ ከባድ ጥፋቶች ተብለው ከተጠቀሱት ወይም ቀላል ጥፋቶችን በተደጋጋሚ ሲፈፅም እና ከደረጃ ዝቅ ሊያደርገው የሚችለውን ጥፋት አንዱን ፈጽሞ ሲገኝ በሥነ ሥርዓት (ዲሲፕሊን) ኮሚቴ ተጣርቶ ጥፋቱ ሲረጋገጥ የሚወሰድ የሥነ ሥርዓት እርምጃ ነው፡፡

2.24 **"ተወካይ"** ማለት አንድ ሠራተኛ በተለያዩ ምክንያቶች ለተወሰነ ጊዜ ከሥራው ሲለይ በምትኩ የሥራ መደቡን በመወከል ከያዘው ሥራ ጋር ደርቦ እንዲሰራ ከውስጥ የሚመደብ ሠራተኛ ነው፡፡

2.25 **"ተጠባባቂ"** ማለት አንድ ሠራተኛ በተለያዩ ምክንያቶች ለዘለቄታው ከሥራ መደቡ ሲነሳ ወይም በቋሚነት ክፍት የሆኑ በቦታው ላይ ሠራተኛ እስኪመደብ ድረስ ክፍት ለሆነው የሥራ መደብ ዝቅተኛ ተፈላጊ መስፈርት የሚያሟላ ወይም የሥራ መደቡ ከሚፈልገው ዝቅተኛ ተፈላጊ የሥራ ልምድ አንድ አመት የቀረው በጊዜያዊነት ቦታው ሽፍኖ የሚሰራ ሠራተኛ ነው፡፡

2.26 **"ትርፍ ሰዓት"** ማለት የትርፍ ሰዓት ማለት ከመደበኛ ሥራ ሰዓት በተጨማሪ ሲሰሩ የሚከፈል ክፍያ ማለት ነው፡፡

2.27 **"የሌሊት አበል ክፍያ"** ማለት ከምሽቱ 4:01 እስከ ንጋቱ 12:00 ድረስ ለሚሠሩ የፈረቃ ሠራተኞች የሚከፈል አበል ነው፡፡

## አንቀጽ 3
## የሕብረት ስምምነት ዓላማ

3.1 የዚህ የሕብረት ሥምምነት ዓላማ በኮርፖሬሽኑ፣ በኮርፖሬሽኑ ሠራተኞችና በማህበሩ መካከል ሁልጊዜም መልካም ግንኙነት እንደተጠበቀ እንዲኖር በማድረግ የኢንዱስትሪ ሰላምን ለማስጠበቅ፣ እንዲሁም ኮርፖሬሽኑና ሠራተኛው ተስማምተው የሚቀበሏቸው የተሻሉና ምቹ የሥራ ሁኔታዎች እንዲኖሩ ለማድረግ፣

3.2 በኮርፖሬሽኑ ውስጥ የኢንዱስትሪ ሰላም እንዲሰፈን፣ ቅን አመለካከት እና ጤናማ የሥራ ግንኙነት እንዲኖር/እንዲዳብር፣ የኮርፖሬሽኑና ሠራተኛው መብትና ግዴቸውን አውቀውና አክብረው በአንድነት ሥራቸውን እንዲያከናውኑና ግንኙነታቸውንም እንዲያጠናክሩ ለማድረግ፣

3.3 ሠራተኛው በመልካም ሥነ-ምግባር ታንፆ፣ ለሥራው ያለውን ፍላጐትና ፍቅር በማጠናከር ምርታማነቱን እንዲያሳድግ፣ በኮርፖሬሽኑም ሆነ ማህበሩ ሠራተኛን እንዲያነቃቁና እንዲያበረታቱ ለማድረግ፣

3.4 ሠራተኛው የኮርፖሬሽኑን ህልውና እና ትርፋማነት የህልውናው መሠረት መሆኑን የኮርፖሬሽኑ ውጤታማነትና ህልውና የሠራተኛው እንደሆነ እንዲገነዘብ ማድረግ ሠራተኛውም ጤንነቱ የሚጠበቅበትን፣ አእምሮውና አካሉ የሚዳብርበትን፣ ለሥራው ተመጣጣኝ ክፍያ አግኝቶ የመኖር ዋስትናው የሚረጋገጥበትን፣ ሰብዓዊ ክብሩ የሚጠበቅበትንና በኮርፖሬሽኑ አስተዳደር የሚሳተፍበትን ሁኔታ መፍጠር፣

3.5 ሠራተኛው እያደገ በሚሄደው የባቡር መሠረተ ልማት ዝርጋታና ትራንስፖርት አገልግሎት የኮርፖሬሽኑን መልካም ስምና ህልውና አስጠብቆ በዓለም አቀፍ ደረጃ በተሻለ ደረጃ ላይ እንዲገኝ ለማድረግ፣

3.6 የኮርፖሬሽኑ የባቡር ትራንስፖርት አገልግሎት ጥራቱ፣ ደህንነቱና ብቃቱ የተሟላና ከአደጋ ነፃ እንዲሆን ማስቻል፣

3.7 ኮርፖሬሽኑ አገልግሎቱን ለደንበኞቹ በተቀላጠፈና በዘመናዊ መልክ ለመስጠት እንዲችል፣ እንዲሁም ተስማሚ የሆኑ የሥራና የአገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታዎችን በመፍጠር ኮርፖሬሽኑ ለተቋቋመበት መሠረታዊ ዓላማ ከግቡ ለማድረስ ነው፡፡

3.8 የማንኛውም የሥራ ውጤት ምንጭና መሠረት ሠራተኛ በመሆኑ የሥራ ሞራሉ ሰብዓዊ መብቱና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሙ ተከብሮ ክብረ ህሊናውና ደህንነቱ ተጠብቆ ሙሉ ኃይሉንና ሙያውን አቀናጅቶ በሥራ ላይ እንዲያውል፣

3.9 በኮርፖሬሽኑ የዕድገት እና የልማት ዕቅድ ውስጥ ሠራተኛውን በማሳተፍ ሀገርን በመገንባት በማጠናከሩ ረገድ የድርሻውን እንዲያበረክት፣

3.10 ሥራ ባህሪው ማህበራዊ በመሆኑ ሠራተኛው ለራሱ ህልውና ሲጣጣር በኮርፖሬሽኑ ብሎም ለሀገሪቱ ብልጽግና እና ዕድገት ኃይልና መሠረት መሆኑን ተረድቶ ስራውን ጥራት ባለው መንገድ አከናውኖ ልማቱን እንዲያፋጥን፣

3.11 በመልካም ሥነ-ምግባር ታንፆ ለሥራው ያለውን ፍላጎትና ፍቅር በማጠናከር ምርታማነቱን እንዲያሳድግ ኮርፖሬሽኑም ሆነ መሠረታዊ የሠራተኛ ማህበሩ ሠራተኛውን እንዲያበረታቱ ለማድረግ፣

3.12 በኮርፖሬሽኑ እና በሠራተኛው መካከል የኢንዱስትሪ ሠላም እንዲሰፍን፣ በመካከላቸው ቀና አመለካከት እንዲኖርና ሁለቱም ወገኖች (አሠሪና ሠራተኛ) ኃላፊነታቸውንና ግዴታቸውን አውቀው፣ አክብረው በአንድነት ሥራቸውን እንዲያከናውኑ እና ግንኙነታቸውንም እንዲያጠናክሩ ለማድረግ ነው፡፡

3.13 የሠራተኛውን ጥቅም ለማስከበር ተስማሚ የሆኑ የሥራ ሁኔታዎች ተፈጥረው ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመበት መሠረታዊ ዓላማ ከግቡ ለማድረስ ነው፡፡

## አንቀጽ 4

## ለሠራተኛ ማህበር ዕውቅና ስለመስጠት

በዚህ ሕብረት ስምምነት ውስጥ ስለተመለከቱት ድንጋጌዎችና ለስራ ሁኔታዎች ሠራተኛውን ወክሎ ከኮርፖሬሽኑ ጋር ለመነጋገርም ሆነ የሕብረት ስምምነት ተደራድሮ ለማስፈፀም የሚያስችለው መሠረታዊ ማህበር መሆኑን ኮርፖሬሽኑ ዕውቅና ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ 5

## የሕብረት ስምምነቱ የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ የሕብረት ስምምነት በኮርፖሬሽኑ ቋሚ እና ጊዜያዊ ሠራተኛ ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፣ ሆኖም በተለየ ሁኔታ ኮርፖሬሽኑን ለማገልገል በኮንትራት የተቀጠሩ ትውልደ ኢትዮጵያን ሆነ የውጭ ዜጎችን እንዲሁም በልዩ ሙያቸው ወይም ልምድ ምክንያት በጊዜያዊነት የተቀጠሩ ሠራተኞችን አያካትትም፡፡

## አንቀጽ 6

## 6. የኮርፖሬሽኑ፣የሠራተኛውና የማህበሩ መብትና ግዴታዎች

### የኮርፖሬሽኑ መብቶች

6.1 በዚህ ስምምነት ውስጥ በሌላ አኳኋን እንዲፈፀም በግልጽ ተለይቶ ካልተወሰነ በቀር አግባብነት ባላቸው የሀገሪቱ ህጎችና ደንቦች ከተዘረዘሩት መብቶች በተጨማሪ አግባብ ባላቸው የኮርፖሬሽኑ የሠራተኞች ወይም ወኪሎች የሆኑ ሠራተኞች አማካይነት የኮርፖሬሽኑን ሥራ የማቀድ፣ የመቆጣጠርና የመምራት፣ ሠራተኞችን የማስተዳደር የመቆጣጠር፣ የመቅጠር፣ እድገት የመስጠት፣ ከሥራ ደረጃ ዝቅ የማድረግ፣ የማዛወር፣ ከሥራ የማገድ፣የባሥነ ስርዓት እርምጃዎችን የመውሰድና አስፈላጊ ሆኖሲገኝ የሠራተኛ

ቅነሳ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ተግባራዊ ማድረግ ወይም ከሥራ የማሰናበት መብቶች ለኮርፖሬሽኑ የተጠበቁ ናቸው፡፡

6.2 የኮርፖሬሽኑን ደንቦችና ድንጋጌዎች የመወሰን፣ ለማውጣት፣ ለማሻሻል፣ ለማቋቋም፣ ለመመደብ፣ ለመለወጥ፣ ለመሠረዝ፣ የደመወዝ ተመን ወይም ሌላ ክፍያ የመወሰን መብት ለኮርፖሬሽኑ የተጠበቀ ነው፡፡

6.3 ኮርፖሬሽኑ በአዋጅና በዚህ የሕብረት ስምምነት የተቀመጡ የሠራተኛ መብቶችን እስካልተቃረነ ድረስ እንደ ሥራው ሁኔታ በፈረቃ ወይም በትርፍ ሰዓት የማሰራት መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

## የኮርፖሬሽኑ ግዴታዎች

6.4 ኮርፖሬሽኑ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ 377/96፣ አዋጅ ቁጥር 494/98 እና ይህን የሕብረት ስምምነት ያከብራል፣

6.5 ለሠራተኛው ጤና አጠባበቅና ከአደጋ ለመከላከል አስፈላጊ የሆኑትን የደንብ ልብሶች እና የሥራ መገልገያዎችን ኮርፖሬሽኑ ሥራው በሚጠይቀው መሠረት ያዘጋጃል፣ የደህንነት መጠበቂ መሳሪያዎች ሲያስፈልጉ በሴፍቲ ማንዋል መሰረት ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

6.6 የማህበር አባል ከሆኑ ሠራተኞች ደመወዝ ላይ ሠራተኛው በጽሁፍ ሲስማማና ይህም ማረጋገጫ ከማህበሩ በአባሪነት ሲተላለፍለት ኮርፖሬሽኑ የማህበሩን መዋጮ በየወሩ በመቀነስ ለማህበሩ ገቢ ያደርጋል፣

6.7 ኮርፖሬሽኑ ሠራተኛ ሲቀጥር የተጠና እና የፀደቀ የሥራ መዘርዝር ከቅጥር ደብዳቤ ጋር ለእያንዳንዱ ሠራተኛ የሚሠራውን ሥራና የኃላፊነቱንም ወሰን የሚያሳይ የሥራ ዝርዝር ይሰጣል፣

6.8 ኮርፖሬሽኑ በመደበኛ የሥራ ሰዓት መውጪያ እና መግቢያ የትራንስፖርት አገልግሎት በአይነት ወይም በገንዘብ ይሰጣል፣

6.9 ኮርፖሬሽኑ ከማህበሩ ጋር በመነጋገር የሠርቪስ አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት እና የሠርቪስ አገልግሎት መስመር ይወስናል፣

6.10 ኮርፖሬሽኑ ለሠራተኛው ለሥራ የሚያስፈልገውን ማንኛውም መሣሪያና ግብዓት በወቅቱ ያቀርባል፣

6.11 ኮርፖሬሽኑ ከሠራተኛ ማህበሩ ጋር በጋራ በመሆን ባለው በጀትና ዕቅድ መሠረት የሠራተኞችን አዕምሯዊ ወይም አካላዊ አቋማቸውን ለማዳበር የሚያስችል የእረፍት ጊዜ ማሳለፊያ የስፖርት መዝናኛ ስፍራዎችን ያዘጋጃል፣

6.12 ኮርፖሬሽኑ በሚገኝበት የሥራ ቦታ የተሟላ ቤተ-መጻሕፍት፣ ቢሮ፣ የቢሮ መገልገያ መሣሪያዎች፣ መፀዳጃ ቤት ያዘጋጃል፣

6.13 የልብስ መለወጫ ስፍራ እንዲሁም አስፈላጊ የሆኑ ማረፊያ ቦታዎችን ያዘጋጃል፣ በኮርፖሬሽኑ በሚወጣ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ መሠረት ዓመታዊ በዓል ያዘጋጃል፡ ፡ በዚህም በዓል ላይ ሠራተኞች በመልካም ግንኙነትና በወንድማማችነት የሚያከብሩበት ዕለት ይሆናል፡፡ በተጨማሪም የሥራ ውድድር ዓላማን በተግባር በመተርጎም ሠራተኞቹ ያላቸውን ዕውቀት፣ አቅምና የፈጠራ ችሎታ ከፈቃደኝነት በመነጨ ስሜት ሙሉ በሙሉ በሥራ ላይ እንዲያውሉ ምርታማነት እንዲያድግና አዳዲስ የአሠራር ዘዴዎች እንዲፈጠሩ ለማነሳሳት፣ ለማበረታት እንዲቻል በሥራው ከፍተኛ ውጤት ላስገኘ ወይም ላስገኙ ሠራተኞች የምስጋና ደብዳቤ ወይም ሽልማት የሚሰጥበት ዕለት ይሆናል፡፡ በዚህም ቅድመ ዝግጅት ላይ የሠራተኛ ማህበሩን ያሳትፋል እንዲሁም እውቅና እና ድጋፍ ይሰጣል፣

6.14 በዚህ የሕብረት ስምምነት፣ በአዋጅ 377/96 እና 494/98 እንዲሁም አግባብነት ባላቸው የሴፍቲ ማኑዋሎች ላይ ለተጠቀሱት ጥፋቶች ኮርፖሬሽኑ በዚህ ሕብረት ስምምነት፣ በሴፍቲ ማኑዋሎች እና በአዋጁ ላይ ከተጠቀሱት የቅጣት እርምጃዎ ወጪ ሌላ የሥነ ሥርዓት እርምጃ አይወስድም፡፡ ከደረጃ ዝቅ የሚያደርጉና ከሥራ የሚያሰናብቱ ጥፋቶች በቅድሚያ በሥነ ሥርዓት ኮሚቴ ታይተው በዋናው ሥራ አስፈፃሚ ወይም በዋና ሥራ አስፈፃሚ በተወከለ የሥራ ኃላፊ ሲፀድቅ ተፈፃሚ ይሆናል፣

6.15 ኮርፖሬሽኑ ለሠራተኞች የህይወትና የአደጋ 24 ሰዓት መድን ዋስትና ይገባል፣

6.16 ሠራተኛው መብትና ግዴታውን አውቆ ሥራውን እንዲያከናውን ኮርፖሬሽኑ ይህንን ሕብረት ስምምነት አሳትሞ ይሰጣል፣

6.17 ኮርፖሬሽኑ በሥራ ላይ እያሉ ሠራተኞች ላይ ለሚደርሰው አደጋ ወደ ህክምና ተቋም የሚያደርስ ተሽከርካሪ በጊዜው ያቀርባል፣

6.18 በዚህ ሕብረት ስምምነት፣ በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 እና በተሻሻለው 494/98 ተያያዥነት ባላቸው የሰራተኞች ጉዳዮች ላይ ኮርፖሬሽኑ ሠራተኞችን በተመለከተ ከሦስተኛ ወገን ጋር በሚያደርገው ስምምነቶች ላይ ማህበሩን እንዲሳተፍ ያደርጋል፣

6.19 የመሠረታዊ ዕቃዎች ዕጥረት ሲያጋጥም የሠራተኛ ማህበሩ መሠረታዊ ዕቃዎች የሆኑ ለሠራተኛው ለማቅረብ ሲፈልግ ኮርፖሬሽኑ ተሽከርካሪ እና ሌሎች ድጋፎችን ይሰጣል፡

6.20 ማንኛውም ሠራተኛ በራሱ ጥፋት ሳይሆን ከሥራ ጋር ባለው ግንኙነት የኮርፖሬሽኑን ጥቃት ለመከላከል በሚወስደው እርምጃ ምክንያት ተከሶ ጉዳዩ እስኪጣራ ድረስ በቁጥጥር ሥር ከዋለ ኮርፖሬሽኑ ለሠራተኛው ዋስትና ይሰጣል፡ ጠበቃ/የሕግ ባለሙያ ይመድባል፡ ተያያዥ ወጪ ይሸፍናል፡

6.21 አንድ የኮርፖሬሽኑ ንብረት የሆነ ተሽከርካሪ ጭኖ ወይም ሳይጭን መንገድ ላይ አደጋ ቢደርስበትም ሆነ ቢያደርስ፡ ቢበላሽ ኮርፖሬሽኑ ሁኔታውን እንዳወቀ በአፋጣኝ በቦታው ተገኝቶ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፡

6.22 ኮርፖሬሽኑ ሠራተኞች በመንግሥት መመሪያ መሠረት የመኖሪያ ቤት ሲሰሩ አቅም በፈቀደ መጠን ድጋፍ ያደርጋል፡

6.23 ሠራተኞች በዕረፍት ጊዜያቸው የሀገርህን እወቅ ኘሮግራም በዓመት አንድ ጊዜ ሲያዘጋጁና በማህበሩ በኩል ሲጠይቁ ኮርፖሬሽኑ የሠርቪስ አገልግሎት ከነዳጅና ከሹፌር አበል ጋር ይሰጣል፡

6.24 ኮርፖሬሽኑ ሠራተኞች የማህበሩ አባሎች ወይም የማህበር መሪ በመሆናቸው ምክንያት ከሥራ እንዲወገዱ፡ እንዲዛወሩና ደረጃቸው እንዲቀነስ ወይም ማግኘት የሚገባቸውን ዕድገት ወይም ጥቅም እንዲያጡ አይደረግም፡

6.25 ሠራተኛው በዓመት ሁለት ጊዜ የግል ማህደር የማየት መብት አለው፡፡ ነገር ግን በቂ ምክንያት እና አስፈላጊነት ሲኖረው በፅሁፍ ሲያቀርብ የግል ማህደር የማየት መብት አለው፡

6.26 ማህበሩ ሕጋዊ የሆኑ መግለጫዎችን እና ማስታወቂያዎችን ኮርፖሬሽኑ በሚጠቀምበት የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ አሳውቆ ይለጥፋል፡፡ ኮርፖሬሽኑ ከሚጠቀምበት ሰሌዳ ውጪ መለጠፍ የተከለከለ ነው፡፡

6.27 በዚህ ህብረት ስምምነት፡ በሕግ ከተገለፀ ተቀናሽ፡ በፍ/ቤት ትዕዛዝ፡ ያልተወራረደ ቅድሚያ አበልና ደመወዝ ወይም ሠራተኛው በራሱ ፍቃድ እንዲቆረጥ ከፈቀደው በስተቀር ከሠራተኛው ደመወዝ መቆረጥ አይቻልም፡፡ ከላይ ከተጠቀሱት ምክንያቶች በአንዱ ወይም በቀሩት የሚቆረጥ ገንዘብ ሲኖር ወዲያው ተቆራጭ መሆኑን ኮርፖሬሽኑ ለሠራተኛው በጽሁፍ ያሳውቃል፡፡

6.28 የሠራተኞችን የእውቀት አድማስ ለማስፋት ጋዜጦችን መጽሔቶችን የሙያ መጽሐፍቶችንና ሌሎች የትምህርት አዘል መረጃዎች እንዲሁም የተለያዩ መመሪያ ሰነዶች ባለቤትም ሆነ ወደፊት በሚቋቋሙ መጻሕፍት ቤቶች እንዲያገኙ ማድረግ፣

6.29 በሥራ ቦታና አካባቢ የመመገቢያ ቦታና የሻይ ክበብ የማዘጋጀት፡፡

6.30 ሠራተኞች የሚሰሩት ሥራ ሊያስከትልባቸው ስለሚችል አደጋ እንዲሁም በጤንነት ላይ የሚደርስ ጉዳትን ለማስወገድ የሚያስፈልገው ጥንቃቄ ተገቢውን ሥልጠና የመስጠት መመሪያ የተሰጣቸው መሆኑንም የማረጋገጥ፣

6.31 ኮርፖሬሽኑ ቅጥር ሲፈጽም የሚፈለገውን የሰው ኃይል ብዛት፣ ደረጃ፣ ደመወዝ፣ ግልጽ የሆነ የሥራ ልምድ፣ የትምህርት ዝግጅት ከተለያዩ የመረጃ ማስተላለፊያ ዘዴዎች ቢያንስ በአንዱ ማውጣት አለበት፣

6.32 ኮርፖሬሽኑ ለሚያከናውናቸው ሥራዎች ወጥ የሆነ አሠራርና መመሪያ መከተል፣ ውልን በግልጽ ማስቀመጥ እና መፈፀም አለበት፣

6.33 ኮርፖሬሽኑ በተቻለ መጠን የሚሰራውን ሥራ በራስ አቅም ይሰራል፡፡

6.34 ሠራተኞች በተቋሙ ውስጥ በተመጣጣኝ ዋጋ የምግብ አቅርቦት እንዲያገኙ ኮርፖሬሽኑ በእያንዳንዱ ምግብ ላይ የ50% ድጎማ ያደርጋል፣

6.35 ኮርፖሬሽኑ የውስጥ የሰው ሃይል አቅም አሟጦ ለመጠቀም ሠራተኛውን ለማትጋትና ኮርፖሬሽኑን በቀላሉ ትርፍ ለማስገኘት የውጭ ማስታወቂያ ከመውጣቱ በፊት ለውስጥ ሠራተኞች የውስጥ ዕድገትና ዝውውር መፈፀም አለበት፣

6.36 በኮርፖሬሽኑ እና በሠራተኛው መካከል የሚደረግ ጊዜያዊ ቅጥር፣ የትምህርትና የሥልጠና ውል በግልፅ ተፅፎ ለሠራተኛው መስጠት አለበት፣

6.37 ኮርፖሬሽኑ ለማህበሩ ቢሮ፣ ቋሚ እና አላቂ የመገልገያ ዕቃዎችን ያቀርባል፡፡

6.38 በሠራተኞች መካከል በፆታ፣ በጎሣ፣ በፖለቲካ ወይም በሃይማኖት ላይ የተመሰረተ ልዩነት ማድረግ የለበትም፡፡

6.39 ሠራተኛው በተሰጠው የስራ መዘርዝር መስራት እየቻለ በሌላ ሠራተኛ ማሰራት አይችልም፡፡

6.40 ሠራተኛው ኮርፖሬሽኑ የሰጠውን የደንብ ልብስ እና የመኪና ማጽጃ፣ የጽዳት መጠበቂያ ዕቃዎችን ኮርፖሬሽኑ ያቀርባል፡፡

## የሠራተኛ መብቶች

6.41 እንደ አግባብነቱ በግልም ሆነ በማህበሩ አማካኝነት ቅሬታውን ኮርፖሬሽኑ ለማቅረብ ይችላል፡፡

6.42 በዚህ ሥምምነት በሌላ አኳኋን የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ሠራተኛው የደረጃ እድገት ለማግኘት ወይም በተመጣጣኝ ደረጃ ወይም በዝቅተኛ ደረጃ ዝውውር ክፍት የሥራ መደብ እስካለ ድረስ የመጠየቅ፣ መብት አለው፡፡ የሠራተኛው ጥያቄ በአስር ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ምላሽ ያገኛል፡፡ ሆኖም አፈፃፀሙ ኮርፖሬሽኑ በሚያወጣው የሥራ ማስታወቂያ እና የሰው ኃይል አጠቃቀም ዕቅድ መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

6.43 አንድ ሠራተኛ የሥራ መዘርዝሩ በጽሑፍ እንዲደርሰው እና በሥራ መዘርዝሩ የተጠቀሰውን መደበኛ ሥራ እንዲሰራ ይደረጋል፡፡ በቅርብ ኃላፊ ወይም ቀጥሎ ባለ የሥራ ኃላፊ የሚሰጠውን ከሥራ መዘርዝሩ ጋር የተያያዘ ሥራ ግን ይሰራል፡፡ ሆኖም በሥራ መዘርዝሩ ላይ ከተሰጠው ስራ በተጨማሪ ወይም የተለየ ሥራ እንዲሰራ ከመደረጉ በፊት የተሰጠው ተጨማሪ ሥራ በጽሁፍ እንዲደርሰው ሆኖ በግል ማህደሩ ውስጥ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡

6.44 ማንኛውም የኮርፖሬሽኑ ሠራተኛ የሠራተኛው ተሳትፎ በሚሆንባቸው በማንኛውም የኮርፖሬሽኑ እቅድ አወጣጥ፣ የሥራ አፈፃፀም ግምገማዎችና በመሳሠለው ጉዳዮች ላይ በራሱ ወይም በተወካዩች አማካኝነት ቀጥተኛ ተሣትፎ በማድረግ አስተያየቱን በጽሁፍም ሆነ በቃል የመግለጽ መብት አለው፡፡

6.45 ሠራተኛው በማህበር ለመወከል መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡ በማህበሩ የመተዳደሪያ ደንብ መሠረት የመሳተፍ ከማህበሩ ባለስልጠናት ጋር የመወያየት ወይም ክርክር ሲነሳ ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ወይም ኮርፖሬሽኑ እና ማህበሩ ወደተስማሙበት ሶስተኛ አካል ወይም ለፍ/ቤት የማቅረብ መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡

## የሠራተኛ ግዴታዎች

6.46 በዚህ የሕብረት ስምምነት በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ እና በሌሎችምየሠራተኛ ጉዳይ ሕጎች በኮርፖሬሽኑ ፖሊሲና መመሪያና ደንብ በሥራ ውሉና በስራ መዘርዝሩ የተቀመጡትን እንዲሁም ከሥራው ጋር በተያያዘ በኮርፖሬሽኑ የሚሰጠውን የሥራ መመሪያ በሙሉ አክብሮ የመፈፀምና የሚመለከተውን ሥራ በራሱ የመሥራት፣

6.47 ሙሉ ጉልበቱን፣ እውቀቱንና ችሎታውን ሳይቆጥብ የተሰማራበትን ሥራ በትክክል፣ በቅልጥፍናና በብቃት የማከናወን፣ የኮርፖሬሽኑ የሥራ የውጤት እንዲዳብርና ከፍ እንዲል በትጋት በታማኝነትና በጥንቃቄ የመሥራት፣

6.48 በሥራው ላይ ሆኖ ወይም ከሥራ ቦታ ዉጪ በሆነ ስፍራ የኮርፖሬሽኑ መልካም ሥምና ክብር ከሚያስነቅፍ ተግባር የመቆጠብ ወይም ቸልተኝነት ያለማሳየት፣

6.49 ችሎታው እስከሚፈቅድለት ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በስራው ውሉ እና በሥራ መዘርዝሩ መሠረት ከሥራው ጋር በተያያዘ በቅርብ ኃላፊ/ቀጥሎ ባለ ኃላፊ የሚሰጠውን የሥራ መመሪያ ወይም የተመደበበትን ሥራ በሚገባ ጥራት እና በወቅቱ የመፈፀም፣

6.50 ደንበኛ የሕልውናችን መሠረት መሆኑን ተገዝቦ ከሥራው ጋር በተያያዘ መልኩ የኮርፖሬሽኑ ደንበኛ በማንኛውም መልኩ ያለማስቀየም እና ለኮርፖሬሽኑ ደንበኞች ክብር በመስጠት የማስተናገድና የመንከባከብ፣

6.51 በሥራ ባልደረባ ወይም በኮርፖሬሽ ደንበኛ ወይም ባለጉዳይ ላይ ያታዊ ትንኮሳ ያለማድረግ፣

6.52 ኮርፖሬሽኑ በሚያዘው መሠረት በኮርፖሬሽኑ ወጪ በየጊዜው የሚደረገውን የህክምናና የሕመም መከላከያ ምርመራ ከኤች.አይ. ቪ. ኤድስ ምርመራ ውጪ መውሰድ እንዲሁም ስለጤና አጠባበቅና የአደጋ መከላከያ መሣሪያዎችና ዘዴዎች እንዲሁም የደንብ ልብስ በኮርፖሬሽኑ የሚሰጡ መመሪያዎች አክብሮ በጥንቃቄ መፈፀም፣

6.53 ሆነ ብሎ ወይም በእንዝህላልነት በራሱ ወይም በሥራ ጓደኞቹ ወይም በሌሎች ሰዎች ህይወት አደጋ፣ ጉዳት ወይም አስጊ የሆነ ሁኔታን ከሚያስከትሉ ድርጊቶች ሁሉ መቆጠብ፣

6.54 በኮርፖሬሽኑ የሥራ ኃላፊ የሚሰጠውን ደብዳቤም ሆነ የውስጥ ማስታወሻ ወይም የፍ/ቤት መጥሪያዎችን ፈርሞ የመቀበል ግዴታ አለበት፣

6.55 አደጋ ሲደርስ ወይም ኮርፖሬሽኑን ወይም የሥራ ጓደኞቹን ወይም የማናቸውም የባቡር ተሳፋሪዎች ሕይወትና ጥቅም ለመንካት ወይም ለማጥፋት የሚችል አስጊ ሆኔታ ሲፈጠር፣ እርዳታ መስጠት ከሠራተኛው አቅም በላይ ካልሆነ እርዳታ በመስጠቱ

እራሱን ወይም ቤተሰቡን ወይም ንብረቱን ለአደጋ ካላጋለጠ አግባብ ባላቸው የኮርፖሬሽኑ ሠራተኞች ወይም ባለሥልጣኖች መሪነት ሠራተኛው እርዳታ ይሰጣል፣

6.56 የኮርፖሬሽኑ ገንዘብ ወይም ሌላ ማናቸውም ንብረት መሰረቁን፣ መባከኑን፣ መጥፋቱን ወይም ያለአግባብ መዋሉን ያየ ወይም ያወቀ ወይም እጅ ከፍንጅ የያዘ ሠራተኛ ሁኔታውን ለሚመለከተው የኮርፖሬሽኑ የሥራ መሪ ወይም ለኮርፖሬሽኑ የደህንነት ጥበቃ ወዲያውኑ ማሳወቅ ወይም መጠቆም አለበት፡፡ ሆኖም ሁኔታውን ለኮርፖሬሽኑ ተጠሪዎች ለማሳወቅ ካልተቻለና የድርጊቱም ዓይነት ወዲያውኑ እርምጃ የሚያስፈልገው ከሆነ በቅርብ ለሚገኝ አግባብ ላለው መንግሥታዊ ወይም ሕዝባዊ አካል ማሳወቅ ወይም መጠቆም አለበት፡፡

6.57 ማንኛውም ሠራተኛ በአዋጁ፣ በዚህ የሕብረት ሥምምነት፣ ወይም በኮርፖሬሽኑ ፖሊሲና ደንብ የተከለከሉ ተግበራትን ከመፈፀም መቆጠብ አለበት፡፡ በተለይም የሚከተሉትን መፈፀም አይችልም፡፡

6.58 አግባብ ባለው የኮርፖሬሽኑ የሥራ መሪ/ኃላፊ ሳይፈቀድለት ማንኛውንም የኮርፖሬሽኑን ወይም በኮርፖሬሽኑ ቅጥር ግቢ የሚገኝ ንብረት ወይም እቃ ለግል ወይም ለሦስተኛ ወገን ጥቅም ማዋል፣ ማውጣት ወይም መውሰድ አይችልም፡፡

6.59 በኮርፖሬሽኑ ሥራ ላይ ያሉትን ሠራተኞች በሚያውክና በሚረብሽ ጉዳትና ጥፋት በሚያመጡ ትክክል ባልሆነ ሁኔታ ወይም በራሱ በፈጠረው መጥፎ ሁኔታ ላይ ሆኖ በሥራ ላይ መገኘት አይችልም፡፡

6.60 በኮርፖሬሽኑ ቅጥር ግቢ ውስጥ በማናቸውም ግለሰብ ላይ መዛት ወይም ማናቸውንም ግለሰብ መስደብ፣ መዝለፍ ወይም መምታት አይችልም፣

6.61 በኮርፖሬሽኑ ፖሊሲዎች ደንቦችና ሥርዓቶች ድንጋጌዎች ወይም የዚህን ስምምነት ግዴታዎች መጣስ ወይም መተላለፍ አይችልም፣

6.62 በሥራው አጋጣሚ ያገኘውን ኮርፖሬሽኑ ምስጢር፣ የባቡር ስምሪት ወይም የጥገና ሙያ ማከናወኛ ደንብና ማንዋሎችን ለግል ጥቅም መገልገያ ወይም ማግኛ አያደርግም፣ የኮርፖሬሽኑንም ሆነ የደንበኞችን ምስጢር ወይም መረጃ ጉዳዩ ከሚመለከተው ሕጋዊ አካል በስተቀር ለሌላ ወገን ለመግለጽ አይችልም/አይገልጽም፡፡

## የማህበር መብቶች

6.63 ማህበሩ አግባብ ባላቸው ሕጎች ደንቦችና አዋጆች በተሰጠው መብት መሠረት የሠራተኞችን ጉዳይ ጥቅማ ጥቅሞችና ደህንነት በሚመለከት ከኮርፖሬሽኑ ጋር በዚህ

ህብረት ስምምነት በተደነገገው ሥነ ሥርዓት መሠረት የመወያየት መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

6.64 በዚህ ስምምነት በተቀመጠው መልኩ ሠራተኛው ማህበሩ በኮርፖሬሽኑ አስተዳደር እንዲሳተፍ ይደረጋል፡፡

6.65 በህብረት ስምምነት ድርድር ወቅት በሠራተኛው በኩል ለመነጋገር የሚችሉትን በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ስምምነቱን ለማድረግ ስልጣን ያላቸው የማህበሩ መሪዎች ናቸው፡፡

6.66 ከማህበሩ ሥራ አስፈፃሚ አባላት፣ የምክር ቤት አባላት የክፍል ተጠሪዎች እና የኦዲት ኮሚቴ አባላት ዉጪ ለማህበሩ በአዋጅ ወይም በዚህ ህብረት ስምምነት የተሰጡትን ተግባራት ወይም መብቶች ለማከናወን አይችልም፡፡

6.67 በዚህ የሕብረት ስምምነት ያልተካተቱ የሠራተኛ መብት የሚመለከቱ ጉዳዮች ለኮርፖሬሽኑ ማሻሻያ ጥያቄውን በማቅረብ በሕብረት ስምምነቱ እንዲካተት የመጠየቅ የመከታተልና የማስፈፀም መብት አለው፡፡

6.68 ማህበሩ በቅጥር፣በዝውውር፣በዕድገት፣የሥነ ሥርዓት ኮሚቴ በሚሰበሰብባቸው የሥነ ሥርዓት እርምጃዎች፣ሠራተኛን በተመለከተ የሚኖሩ የካፍቴሪያ አስተዳደር ጉዳዮች፣ በሥልጠና፣በትምህርት፣በኮርፖሬሽኑ ዕቅድ አወጣጥ እና መዋቅር አዘገጃጀት ላይ ተሳትፎ ይኖረዋል፡፡

## የማህበር ግዴታዎች

6.69 ማህበሩ የኮርፖሬሽኑን ፖሊሲና ደንቦችን እንዲሁም መመሪያዎችን የአሠሪና ሠራተኛ አዋጁንም ሆነ ሌሎች የሠራተኞች ጉዳይ ህጎችን እና ይሕንን ስምምነት የማክበር፣

6.70 ማህበሩ በአዋጅ ውስጥ የተከለከሉ ወይም ከዓላማውና ከመተዳደሪያው ደንብ ውጭ የሆነ ተግባራት እንዳይፈፀሙ የመከላከልና እነዚህ አድራጎቶችን ለማረምና ለማስወገድ ከኮርፖሬሽኑ ጋር በመመካከር በጋራ የመሥራት፣

6.71 የአሰሪና ሠራተኛ ደንቦች ሕጎችና መመሪያዎችና መግለጫዎች እንዲሁም የዚህ ህብረት ስምምነት ድንጋጌዎች እንዲታወቁና እንዲከበሩ የማድረግና የማስተማር፣

6.72 የኮርፖሬሽኑ ሠራተኞች የሚመለከቱ ሕጎች ደንቦችን ማመንጨት፣ሲዘጋጁና ሲሻሻሉ ሀሳብ የማቅረብ፣

6.73 ለኮርፖሬሽኑ እድገትና ትርፋማነት የሠራተኞች የሥራ ሁኔታዎች ስለሚሻሻሉበት ሁኔታ፣በኮርፖሬሽኑና ሠራተኛው መካከል ጤናማና የተሻለ ግንኙነት ስለሚኖርበት ሁኔታ ከኮርፖሬሽኑ ጋር በመመካከር በሕግ አግባብ የመስራት ግዴታ እና የማህበሩን የሥራ አስፈፃሚ አባላት፣የምክር ቤት አባላት የኦዲት ኮሚቴ እና የክፍል ተጠሪዎችን ሥም ዝርዝር በጽሁፍ ለኮርፖሬሽኑ የማሳወቅ ግዴታ ይኖርበታል፣

## የጋራ ውይይትና ግንኙነት

6.74 የጋራ ምክክር ውይይት ዓላማ የሠመረ የሥራ ግንኙነት ተመሥርቶ በኮርፖሬሽኑና በማኅበሩ መካከል ያለውን ግንኙነት በማጠናከር የሥራ ምርታማነት እንዲዳብር ማድረግ ነው፡፡

6.75 በዚህ ስምምነት፣ በኮርፖሬሽኑ ፖሊሲዎችና ደንቦች ወይም ልማዳዊ አሠራሮች ትርጉም ላይ ወይም አብዛኛውን ሠራተኛ በሚመለከት ጉዳይ ላይ ውይይት ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣በኮርፖሬሽኑ ወይም በማኅበሩ ጥያቄ በየወሩ የመጨረሻ ሐሙስ ወርሀዊ ስብሰባ ለማድረግ ይቻላል፡፡ የተባለው የመጨረሻ ሀሙስ የበዓል ቀን ቢሆን ስብሰባው በሚቀጥለው ቀን ይሆናል፡፡ ስብሰባው በአንደኛው ወገን ጥያቄ ከአንድ ጊዜ በላይ አይተላለፍም፡፡ የወል ከሆኑት በስተቀር የግል ቅሬታዎች በዚህ ስብሰባ ላይ አይነሱም፡፡

6.76 የሠራተኛ ማህበሩ ከኮርፖሬሽኑ ጋር የሚያደርጋቸው የደብዳቤ ግንኙነቶች ኮርፖሬሽኑ የሰው ሀብት ልማት መምሪያ ጋር ይሆናል፡፡ኮርፖሬሽኑ እንዲሁ ከሠራተኛ ማህበሩ ጋር የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች በኮርፖሬሽኑ የሰው ሀብት ልማት መምሪያ በኩል የሆናል፡፡ ማህበሩ እንደአስፈላጊነቱ ከሚመለከታቸው የሰው ሀብት ም/ዋ/ሥራ አስፈፃሚ ወይም የዋና ሥራ አስፈሚውን ትኩረት ብቻ የሚሹ ጉዳዮች ሲያጋጥሙት በቀጥታ ከሰው ኃብት ም/ዋ/ሥራ አስፈፃሚ ወይም ከዋና ሥራ አስፈሚው ጋር የደብዳቤ ግንኙነት ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ልዩ/አስቸኳይ ስብሰባ

6.77 ከሚቀጥለው የወር ስብሰባ በፊት አስቸኳይ በሆኑ ጉዳዮች ላይ መወያየት ሲያስፈልግ በኮርፖሬሽኑ ወይም በማኅበሩ ጥያቄ በዓመት ውስጥ አምስት ልዩ ስብሰባዎች ማድረግ ይቻላል፡፡አስፈላጊ ከሆነና ሁለቱም ወገኖች ከተስማሙ ተጨማሪ ልዩ ስብሰባዎች ማድረግ ይቻላል፡፡

6.78 ስብሰባው የሚደረግበት ጊዜ ሁለቱ ወገኖች በሚያደርጉት ስምምነት ይወሰናል፡፡

6.79 በስብሰባው ላይ የሚገኙት ከሁለቱም ወገን በቀረበው አጀንዳ ላይ በዚያው ስብሰባው ውሳኔ መስጠት የሚችሉ ባለሥልጣኖች መሆን አለባቸው፡፡

6.80 በምክክር ስብሰባ ላይ ከኮርፖሬሽኑ ሦስት ተወካይ ከማህበሩ ሦስት ተመራጭ በላይ መቅረብ የለበትም፡፡ ሆኖም እንደ አስፈላጊነቱ እና እንደ አጀንዳዎቹ ክብደት እየታየ እስከ 10 የማህበሩ መሪዎች ሊገኙ ይችላሉ፡፡

6.81 ስብሰባው ከመደረጉ ቢያንስ ከአንድ ሳምንት በፊት ኮርፖሬሽኑና ማኀበሩ የውይይቱን አጀንዳ ይለዋወጣሉ፡፡ ሁለቱም ወገኖች ካልተስማሙ በስተቀር በአጀንዳው ላይ ባልሰፈሩ ጉዳዮች ላይ ውይይት አይደረገም፡፡

6.82 ማንኛውም ወገን እንደ አስፈላጊነቱ የሕግ አማካሪውን፡ ምሥክሮች ወይም ማስረጃዎች ይዞ መቅረብ ይችላል፡፡

6.83 በአጀንዳው ላይ የተጠቀሱት ጉዳዮች በዕለቱ ስብሰባ ካልተጠናቀቁ ስብሰባው በማግሥቱ ይቀጥላል፡፡

6.84 የስብሰባው ቃለ ጉባኤ ውሳኔ ወይም ስምምነት ስብሰባው ባለቀ በአምስት የሥራ ቀን ውስጥ በኮርፖሬሽኑ ወይም በማህበሩ እንደሁኔታው ተዘጋጅቶ ለሁለቱም ወገን ባለሥልጣኖች ፊርማ ይቀርባል፡፡

6.85 በዚህ ዓይነት ስብሰባዎች ስምምነት የተደረሰባቸው ጉዳዮች በሁለቱም ወገኖች ተፈርመው ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡ ሆኖም ስምምነቶቹ ህብረት ስምምነቱን የሚቀይሩ ወይም የሚያሻሽሉ ወይም አዲስ የስራ ሁኔታ የማፈጥሩ ከሆነ በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከተመዘገበ በኋላ የኀብረት ስምምነቱ ተጨማሪ አካል ይሆናል፡፡

6.86 የአስቸኳይ ስብሰባው የስብሰባ ስነ-ሥርዓት ከንዑስ አንቀጽ 6.76 እስከ 6.84 ድረስ በተገለፀው መሠረት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 7

## የቋሚ ሠራተኛ ቅጥርና የሙከራ ጊዜ

7.1 የአዲስ ሠራተኛ ቅጥር በአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96፡494/98 (ማሻሻያ) እና በዚህ ሕብረት ስምምነትና አስተዳደር መመሪያ መሠረት ይፈፀማል፡

7.2 ማንኛውም አዲስ ቋሚ ሠራተኛ የሙከራ ጊዜ 45 ቀናት ይሆናል፡፡ በቋሚ ቅጥር የተቀጠረ ሠራተኛ ከ45 ተከታታይ ቀናት በኋላ የቋሚነት ማረጋገጫ ደብዳቤ ይደርሰዋል፡፡ ባይሰጠውም ቋሚ እንደሆነ ይቆጠራል፡

7.3 በሙከራ ላይ ያለ ሠራተኛ የሥራ ድርሻውንና ኃላፊነቱን አሟልቶ እንዲያውቅ ኮርፖሬሽኑ የሥራ ትውውቅ ገለፃ ይሰጠዋል፣

7.4 በሙከራ ላይ ያለ ሠራተኛ የሙከራ ጊዜው በበቂ ሁኔታ ባለማጠናቀቁ ቢሰናበት የዓመት ዕረፍት ፈቃድና ማናቸውንም የጥቅማጥቅም ክፍያ አያገኝም፣

7.5 ማንኛውም ጊዜያዊ ሠራተኛ የሙከራ ጊዜ አይኖረውም፣ነገር ግን ኮርፖሬሽኑ በቋሚ የሥራ መደብ ላይ ጊዜያዊ ሠራተኛን ከአንድ ዓመት በላይ የሚያሠራው ከሆነ ቋሚ ይሆናል፣

7.6 በሙከራ ላይ በሚገኙ ሠራተኞች በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 የተደነገጉ የሥራ ሁኔታዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል፣

7.7 በዚህ ስምምነት በኮርፖሬሽኑ ፖሊሲ ከተቀመጡት ግልጽ ድንጋጌዎች በስተቀር በዚህ ህብረት ስምምነት የተቀመጡት በሙከራ ጊዜ ላይ ያለን ሠራተኛ አይመለከተውም፡፡

7.8 ሠራተኛው በውሉ መሠረት ሥራውን እንዲጀምር ኮርፖሬሽኑ ባለማድረጉ ምክንያት የጠፋው ጊዜ ለሙከራ የተወሰነው ጊዜ ውስጥ ይጠቃለላል፡፡

## አንቀጽ 8
## መደበኛ የሥራ ሰዓት እና የሳምንት ዕረፍት ጊዜ

8.1 መደበኛ የሥራ ሰዓት በቀን 8 ሰዓት በሳምንት ከ48 ሰዓት አይበልጥም፣

8.2 ለቢሮ ሠራተኞች የሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት፣

ሀ. ከሰኞ እስከ ሐሙስ ጧቱ ከ2፡30 እስከ 6፡30 ሰዓት፣

ለ. ዓርብ ጧት 2፡30 እስከ 5፡30 ሰዓት፣

ሐ. ከሰኞ እስከ አርብ ከቀትር በኋላ ከ7፡30 እስከ 11፡30 ሰዓት ይሆናል፣

መ. ከዋናው መ/ቤት ውጭ ባሉ ቦታዎችና ፕሮጀክቶች፣ሳይቶች እና ፈረቃ ሰራተኞች እንደአስፈላጊነቱ ኮርፖሬሽኑና ሠራተኛ ማህበሩ ተነጋግረው የሥራ መግቢያና መውጫ ሰዓት ሊለወጥ ይችላል፣

ሠ. በፈረቃ የሚሰሩ ነፍሰጡር ሴቶች 7 ወር መሙላቱ በሀኪም ከተረጋገጠ የሥራ ሰዓት (ከጠዋቱ 1፡00 — ምሽቱ 12፡00) ባለው ሰዓት ውስጥ እንድትሰራ ይደረጋል፣

8.3 በፕሮጀክት ወይም በኦፕሬሽን ላይ ለሚሠሩ ሠራተኞች የሥራ ሰዓት በሳምንት ከ48 ሰዓት የማይበልጥ ሆኖ በሚወጣው የሥራ ፕሮግራም መሠረት የፈረቃ ጊዜ ይወሰናል፣

LABOUR ASSOCIATION

8.4 በፕሮጀክት እና በኦፕሬሽን ለሚገኙ የኮርፖሬሽኑ ሠራተኞች እንደ አየሩ ፀባይና እንደ አካባቢው ሁኔታ የሥራ ጊዜያቸው በፕሮጀክት ጽ/ቤት በተገለፀ መሠረት እንደአመቺነቱ ይወሰናል፣

8.5 የፈረቃ የሥራ ሰዓት በቀን 8 ሰዓት በሳምንት ከ48 ሰዓት አይበልጥም፣

8.6 የሥራ ሰዓቶች ለሣምንት በኮርፖሬሽኑ የሥራ ቀናት እኩል ይደለደላሉ፡፡ የሥራ ፀባዩ ሲያስገድድ ግን በማንኛውም የሣምንቱ የሥራ ቀኖች የሥራ ሰዓቶች ማሳጠርና ልዩነቱን ለቀሩት ቀናቶች ማደላደል ይቻላል፡፡ ሆኖም የማንኛውም የሥራ ቀን መደበኛ የ8 ሰዓት ገደብ ከሁለት ሰዓት ለበለጠ ጊዜ ማራዘም አይቻልም፡፡

## አንቀጽ 9

## የትርፍ ሰዓት ሥራ

9.1 ማንኛውም ሠራተኛ አንቀጽ 8 ከተወሰነው መደበኛ የዕለት ወይም የሣምንት የሥራ ሰዓት በላይ እንዲሰራ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ 377/96 አንቀጽ 67 መሠረት ኮርፖሬሽኑ ካዘዘው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 68 መሠረት የትርፍ ሰዓት ክፍያ ይከፍላል፣

9.2 ነፍሰጡሮች ከምሽቱ 12፡00 ሰዓት በኋላ እንዲሰሩ አይገደዱም፣

9.3 በንዑስ አንቀጽ 9.1 በተጨማሪ የትርፍ ሰዓት ስራ የሚፈቀደው በዋና ሥራ አስፈፃሚ፣ በም/ሥራ አስፈፃሚ ወይም በቢዝነስ ዩኒት ሥራ አስኪያጅ ነው፡፡ ሥራውም ሲጠየቅ የሥራው ዓይነት፣ የሚፈጀው ጊዜና ሰዓት እንዲሰራ የተደረገበት ምክንያት መገለጽ አለበት፣

9.4 ሠራተኛው የሰራበትን የትርፍ ሰዓት ክፍያ ሥራውን በሰራበት ወር ውስጥ ይከፈለዋል፣

9.5 አንድ ሠራተኛ የአየር ፀባይ አበል በሚከፈልበት ቦታ በቋሚነት እየሠራ የትርፍ ሰዓት ሥራ እንዲሰራ ከተገደደ የትርፍ ሰዓት ስሌቱ በመንግስት መመሪያ መሠረት የሚፈፀም ይሆናል፡
፡

## አንቀጽ 10

## ደመወዝ መክፈያ ቀን እና ስለ ደመወዝ አከፋፈል

10.1 የኮርፖሬሽኑ ሠራተኞች በሙሉ በየወሩ እ.ኤ.አ በ26ኛው ቀን ደመወዝ ይከፈላል፡፡ ነገርግን ሥራ ዝግ በሚሆንባቸው ሃይማኖታዊ በዓላት እ.ኤ.አ ከ23 እስከ 25 ባሉት ቀናት ውስጥ የሚከፍል ይሆናል፡፡

10.2 ለማንኛውም ሠራተኛ የተጣራ የወር ደመወዙን በትክክል የሚያሳይ መግለጫ/ስሊፕ/ ኮርፖሬሽኑ በየወሩ ይሰጣል፡

10.3 ለማንኛውም ሠራተኛ ኮርፖሬሽኑ ስራ ባላዘጋጀበት ሁኔታ የሠራተኛው ደመወዝ አይቆረጥም፡

10.4 በሕግ ከተቀመጠ ተቀናሽ፡ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ፡ ሠራተኛው በጽሑፍ ሲስማማ፡ ቅድሚያ የጉዞና የነዳጅ አበል ፈርሞ ወስዶ በወቅቱ ካላወራረደ እና በሕብረት ስምምነት በተጠቀሱ ጉዳዮች ካልሆነ በስተቀር የማንኛውም ሠራተኛ ደመወዝ መያዝ ወይም መቀነስ አይችልም፡

## አንቀጽ 11
## የሥራ አፈፃፀም ግምገማና ዓላማ

11.1 ኮርፖሬሽኑ በሚያወጣው የሥራ አፈፃፀም ምዘና ፖሊሲና መመሪያ መሰረት የሰራተኞች የስራ አፈፃፀም ምዘና የሚፈፀም ይሆናል፡፡

### የሥራ ውጤት መመዘኛ ዓላማ

11.2 የሠራተኞች የሥራ ውጤት በትክክል በመለካት ትጉህ ሠራተኞችን በማበረታታት ጠንካራ ጎናቸውን እንዲጎለብት ለማድረግና መሻሻል በሚያስፈልጋቸው ነጥቦች ላይ ሊሻሻሉ የሚችሉበትን ሁኔታ በመቀየስ የሥራ ውጤታቸውን ከፍ ለማድረግ፡

11.3 ኮርፖሬሽኑ የሚያወጣውን ዕቅድ ግብ እንዲመታ የሥራ መጠንና ጥራት ከፍ እንዲል ለማድረግ አስፈላጊውን ክትትል፡ ቁጥጥርና የእርምት እርምጃ በወቅቱ ለመውሰድ እንዲሁም ዝቅተኛ አፈፃፀም ያላቸውን ሠራተኞች ለመለየትና ልዩ ትኩረትና ስልጠና እንዲያገኙ በማስቻል ብቃታቸውን እንዲያሻሽሉ እድል ለመስጠት፡

11.4 በውጤት ላይ በተመሠረተ ግምገማና ምዘና የሠራተኞችን ምደባና ዕድገት፡ ዝውውር የደመወዝ ጭማሪ፡ ሥልጠና እንዲሁም ሌሎች ተመሳሳይ የሥራ ሁኔታዎችን በትክክል ለመፈፀም የሠራተኞችን የሥራ መንፈስ ለማትጋትና የኮርፖሬሽኑን ሥራ ለማሻሻል፡

### የሥራ ውጤት መመዘኛ ቅጽ ይዘትና አሞላል

11.5 እያንዳንዱ ሠራተኛ በዋናነት የሚመዘነው በተሠጠው የሥራ መዘርዝር መሰረት በበጀት ዓመቱ ካስቀመጠው ዕቅድ ጋር በማነፃፀር ይሆናል፡

11.6 ኮርፖሬሽኑ ሠራተኛን የመሚዝንበት መስፈርት ከሠራተኛ ማህበሩ ጋር በመሆን ያዘጋጃል፡ ፡

11.7 የሥራ ኃላፊ ወይም የቅርብ ኃላፊ በሥሩ የሚገኙትን ሠራተኞች የሥራ ውጤት የሚለካው በቅጹ ላይ በሰፈሩት የመመዘኛ መስፈርቶች ብቻ ይሆናል፡

11.8 የሥራ ኃላፊ ወይም የቅርብ ኃላፊ ከተመዛኙ ሠራተኛ ጋር ባለው የግል ትውውቅ ወይም ጥላቻ፡የጥቅም ግንኙነት ወይም የቀድሞ የምዘና ውጤትን መሠረት በማድረግ ብቻ የተመዛኙን ሠራተኛ ውጤት ከፍ ወይም ዝቅ ማድረግ አይችልም፡፡

### የምዘና ወቅት

11.9 እያንዳንዱ ሠራተኛ በዓመት ሁለት ጊዜ የሥራ ውጤቱ መመዘን አለበት፡

11.10 የምዘና ወቅቶች በሁለት የተከፈሉ ሲሆን ይኸውም ከሐምሌ 1 እስከ ታህሳስ 30 ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከጥር 1 እስከ ሰኔ 30 ድረስ ይሆናል፡፡

### የሠራተኛ የሥራ ውጤት መግለጫ ከላይ እንደተገለፀው ከተሞላ በኋላ

11.11 የሠራተኛው የቅርብ ኃላፊ ሥራ ምዘና አፈፃፀም ይሞላል፡ በሥራ ውጤቱ ያልተስማማ ሠራተኛ ቅሬታውን ለሚቀጥለው ኃላፊ አቅርቦ የሚቀጥለው ኃላፊ ገምግሞ ውሳኔ ይሰጥበታል፡

11.12 በዚሁ መሠረት በሥራ አፈፃፀም ግምገማ ላይ ሠራተኞች ቅሬታ ካቀረቡ የሥራ ምዘና ከሞላውና የሥራ ውጤት ካፀደቀው የሥራ ኃላፊ በተጨማሪ በቀጣይ ደረጃ የሚገኝ የሥራ ኃላፊ ታይቶ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጠዋል፡፡ ሆኖም ሠራተኛው በውሳኔው ቅሬታ ቢኖረው በዚህ ሕብረት ስምምነት የቅሬታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት ወይም በኮርፖሬሽኑ የቅሬታ አቀራረብ መመሪያ መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

11.13 የሠራተኛውን የሥራ አፈፃፀም የበላይ የሥራ ኃላፊው የሚሞላው የቅርብ ኃላፊው መሙላት በማይችልበት ጊዜ እና ከሠራተኛው ጋር በማይስማሙበት ብቻ ነው፡

11.14 አንድ ሠራተኛ በተለያዩ ምክንያቶች ከሚሠራበት ክፍል ወደሌላ የሥራ ክፍል በጊዜያዊነት ተዛውሮ ከሰራና ወደ ቀድሞ የሥራ ክፍሉ ሲመለስ በቆይታ ጊዜ የነበረውን የሥራ አፈፃፀም የሚገልጽ ደብዳቤ ተዘጋጅቶ ለክፍሉ ወዲያውኑ ይላካል፡፡ ክፍሉም የሥራ አፈፃፀሙ የሚመዝነው ኮርፖሬሽኑ በሚጠቀምበት የጊዜ ሠሌዳ ሆኖ አብዛኛውን የሥራ ጊዜ የሰራበት የሥራ ክፍል ቀድሞ/በኋላ የሠራበትን የሥራ አፈፃፀም ግብዓት በመውሰድ የሚመዝን ሲሆን ተመጣጣኝ (እኩል) ጊዜ በሁለቱም ክፍሎች ውስጥ ከሰራ በወቅቱ እየሰራ ያለበት የሥራ ኃላፊ ቀደም ሲል ይሰራበት ከነበረበት ክፍል የነበረውን የሥራ አፈፃፀም ግብዓት በማካተት ሊሞላለት ይገባል፡

11.15 ማንኛውም ሠራተኛ የሥራ አፈፃፀም ምዘና ውጤቱን እንዲያውቀው ይደረጋል፡፡ ሠራተኛው በተሰጠው ውሳኔ ቅር ከተሰኘ በየደረጃው ላሉ የሥራ ኃላፊዎች ቅሬታውን ሊያቀርብ ይችላል፡፡

11.16 አንድ ሠራተኛ የሚመዘነው በስራው ስራ ብቻ ነው፡፡ ነገር ግን ሠራተኛው የግምገማ ጊዜውን በስልጠና፣በህመም ፈቃድ፣በወሊድ ፍቃድ፣ብሔራዊ ግዴታውን በመወጣት ላይ ሆኖ በስራ ምዘና ባለመመዘኑ ምክንያት እንደማንኛውም ሠራተኛ ሊያገኛቸው የሚገባቸው ጥቅማጥቅሞችን አያጣም፡፡ስለሆነም ሠራተኛው የስራ አፈፃፀሙን እንዲያሻሽል ዕድል ይሰጠዋል፡፡በተጨማሪም ሠራተኛው የተሰጠው ዝቅተኛ አፈፃፀም ውጤት እንዲታይ ማህበሩ ከበቂ ምክንያት ጋር ጥያቄ ሲያቀርብ ማኔጅመንቱ ሁኔታውን አጣርቶ ተገቢ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## የሥራ አፈፃፀም ምዘና ውጤት አሞላል ስርዓት

11.17 የሥራ አፈፃፀም ምዘና በግል ስሜት ወይም በአንዳንድ አጋጣሚዎች ሳይመራ በተቻለ ደካማ መጠን በተጨባጭ ሁኔታዎች ላይ በመመርኮዝ የሥራ አፈፃፀም ላይ ያሉ ጠንካራና ጎኖችን በመለየት በጥንቃቄና በትክክል ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ መሠረት ውጤቱ መሞላት አለበት፡፡

ሠንጠረዥ 1፡ የሥራ አፈፃፀም ውጤት ደረጃ

| ተ.ቁ | የሥራ አፈፃፀም ውጤት | የተሰጠ ነጥብ |
|---|---|---|
| 1 | ከ91-100% | የላቀ |
| 2 | ከ70-90% | ጥሩ |
| 3 | ከ60-69% | መካከለኛ |
| 4 | ከ59 በታች | ዝቅተኛ |

11.18 ማንኛውም ሠራተኛ በተከታታይ የሶስት ጊዜ የሥራ አፈፃፀም ውጤቱ መካከለኛ ሆኖ ከተገኘ እና እንደአስፈላጊነቱ አቅም ግንባታ ሥልጠና እንዲሁም በተመሳሳይ የሥራ ደረጃ ዝውውር ተሰጥቶ ሊሻሻል ካልቻለ ከደረጃና ደመወዝ ዝቅ ተደርጎ ሊመደብ ይችላል፡፡ በተመደበበት የሥራ መደብ ላይ አሁንም መካከለኛ አፈፃፀም የሚያሳይ ከሆነ ጉዳዩ ታይቶ ከሥራ ሊሰናበት ይችላል፡፡

11.19 ማንኛውም ሰራተኛ ውጤቱ በተከታታይ ሁለት ጊዜ ዝቅተኛ የስራ አፈፃፀም ውጤት ካገኘ እና እንደአስፈላጊነቱ የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቶት በቀጣይ የስራ አፈፃፀም ምዘና

ዝቅተኛ ውጤት ካስመዘገበ ኮርፖሬሽኑ እስከ ስራ ስንብት የሚደርስ እርምጃ ሊወስድበት ይችላል፡፡

## አንቀጽ 12

## የደመወዝ ጭማሪ እና ማበረታቻ

12.1 የደመወዝ ጭማሪ እና የማበረታቻ ዓላማ የኮርፖሬሽኑን ትርፋማነት ለማረጋገጥ፣ የሠራተኛውን የመሥራት ፍላጎት እና አቅም ይበልጥ ለማሳደግ ነው፡፡ የደመወዝ ጭማሪ ተፈፃሚ የሚሆነው በኮርፖሬሽኑ የሥራ አመራር ቦርድ ሲፀድቅ ነው፡፡

12.2 የደመወዝ ጭማሪ የሚመለከታቸው ለቋሚ እና ጊዜያዊ ሠራተኞች ነው፣

12.3 በኮርፖሬሽኑ የደመወዝ ስኬል መሠረት ጣሪያ ላይ ለደረሰና ከጣሪያ በላይ ለሆኑ ሠራተኞች የደመወዝ ጭማሪ አይደረግም፡፡ ነገር ግን ኮርፖሬሽኑ ሲያምንበት በገንዘብ ወይም በዓይነት ሽልማት፣ የትምህርት ዕድል፣ ምርምር እንዲያካሂዱ፣ በሙያቸው አማካሪ ሆነው ተጨማሪ ክፍያ እንዲያገኙ ኮርፖሬሽኑ በሚያወጣው አስተዳደራዊ መመሪያ ወይም መስፈርት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

12.4 ኮርፖሬሽኑን በልዩ የፈጠራ ሥራ የደገፈ፣ ከኪሳራ፣ ከአደጋ ወይም ከጥፋት ያዳነ፣ የተሻለ የአሠራር ሥርዓት ተግባራዊ በማድረግ ኮርፖሬሽኑን ትርፋማ ያደረገ ሠራተኛ በገንዘብ ወይም በዓይነት ማበረታቻ ይሠጠዋል፣

12.5 የደመወዝ ጭማሪ ለማጽደቅ የኮርፖሬሽኑ የሥራ ዕቅድ አፈፃፀም የሠራተኛውን ነባራዊ የኢኮኖሚ ሁኔታ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ይሆናል፡፡

12.6 ለኮርፖሬሽኑ ሠራተኞች በበጀት ዓመት ተከፍሎ የሚያልቅ የሁለት ወር ደመወዝ በብድር በበጀት ዓመት መጀመሪያ ይሰጣል፣

## አንቀጽ 13

## የአየር ፀባይ አበል

13.1 ቆላ ወይም በረሃ በሆኑ ቦታዎች ተመድበው ለሚሰሩ የኮርፖሬሽኑ ሠራተኞች ቦታው ደርሰው ሥራውን ከጀመሩበት ቀን ጀምሮ የአየር ፀባይ አበል ይከፈላቸዋል፣

13.2 የአየር ፀባይ አበል አከፋፈል በመንግስት መመሪያ መሠረት ተከፋይ ይሆናል፡፡

13.3 ለአንድ ሠራተኛ የአየር ፀባይ የሚከፈለው አበል እንዲከፈል በተወሰነበት የሥራ ቦታ ሠራተኛው ለሚቆይበት ጊዜ ብቻ ነው፡፡ በዝውውርም ሆነ በሌላ ምክንያት ከቦታው ተነስቶ የአየር ፀባይ አበል የማይከፈልበት ሥፍራ ቢመደብ ቀድሞ ይከፈለው የነበረው የአየር ፀባይ አበል ወዲያውኑ ይቋረጣል፡፡

## አንቀጽ 14

## የጉዞ (የውሎ) አበል ተመንና አከፋፈል

14.1 ማንኛውም ሠራተኛ የቀን የውሎ አበል ብር 400.00 (አራት መቶ ብር ብቻ) ይሆናል፡፡ የውሎ አበል አከፋፈል ለቁርስ 10%፣ ለምሳ 25%፣ ለእራት 25% እና ለአልጋ 40% ስሌት መሠረት ነው፡፡ ከተመደበበት የሥራ ቦታ ከጧቱ 2፡00 ሰዓት በኋላ ለሚወጣ የቁርስ አበል አይከፈልም፣ ከቀኑ 6፡00 ሰዓት በፊት የሚመለስ የምሳ አበል አይከፈልም፣ ከምሽቱ 1፡00 ሰዓት በፊት የሚመለሱ ለእራት አበል አይከፈልም፡፡ ሠራተኛው ካላደረም የአልጋ አበል አይከፈልም፣

14.2 ማንኛውም ሠራተኛ በቋሚነት ከተመደበበት የሥራ ቦታ 25 ኪ.ሜ ውጭ ለሥራ ሲላክ ለቆየበት ጊዜ በአንቀጽ 14.1 መሠረት የውሎ አበል ይከፈለዋል፡፡ ነገር ግን ለስልጠና ከሚሰራበት ቦታ ውጪ ከተላከ በአስተዳደር መመሪያ ወይም በትምህርትና ሥልጠና መመሪያ መሠረት ይስተናገዳል፡፡

14.3 በአንቀጽ 14.1 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሠራተኛ የአየር ፀባይ አበል በሚከፈልባቸው የሥራ ቦታዎች ለሥራ ወይም ለሥልጠና ከተላከ ለቦታው የሚከፈለው የአየር ፀባይ አበል በሠራተኛው የውሎ አበል ላይ ታክሎ ይከፈለዋል፡፡

14.4 ኮርፖሬሽኑ በፕሮጀክት ላይ ለሚሰሩ ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ሠራተኞች መጠለያ/ካምፕ/እና ምግብ ያቀርባል ሆኖም እነዚህን ባያዘጋጅ በንዑስ አንቀጽ 14.1 የተቀመጠው ተፈፃሚ ይሆናል፣ ሆኖም ግን የፕሮጀክቶች የጥቅማጥቅም መመሪያ እንደ ፕሮጀክቱ ባህሪ የተዘጋጀ ካለ በመመሪያው መሠረት ይስተናገዳል፡፡

## አንቀጽ 15

## ቅጥር፣ ዕድገት፣ ምደባ እና ውክልና

### አጠቃላይ ሁኔታ

15.1 በኮርፖሬሽኑ ውስጥ በሚገኙ ክፍት የሥራ ቦታዎች የሠራተኛ ቅጥር ለመፈፀም በመረጃ ማስተላለፊያ መንገዶች ጥሪ ከመደረጉ በፊት በመጀመሪያ የኮርፖሬሽኑ ሠራተኞች እንዲያድጉበት የውስጥ ዕድገት ማስታወቂያ በማውጣት፣ በ2ኛ ደረጃ በአንቀፅ 16 መሰረት የዝውውር ቅድመ ሁኔታዎች ሲሟሉ ዝውውር ማስታወቂያ በማውጣት፣ በነዚህ መንገዶች ማሟላት ካልተቻለ በውጭ በቅጥር ሠራተኛ ማሟላት አለበት፡፡

### ዕድገት

15.2 በዚህም የውስጥ ዕድገት ውድድር በኮርፖሬሽኑ ውስጥ ነባር ሠራተኛ ሆኖ የዕድገት ደብዳቤ ካገኘበት ቀን ጀምሮ አንድ ዓመት ካገለገለ በዕድገቱ መወዳደር ይችላል፡፡ አዲስ ሠራተኛ ሆኖ የቅጥር ደብዳቤ ከተሰጠበት አንድ ዓመት ካገለገለ በኋላ በዕድገቱ መወዳደር ይችላል፡ ፡ ነገር ግን ማንኛውም ጊዜያዊ ሠራተኛ ለቋሚ ሠራተኛ በወጣው የውስጥ ዕድገት መወዳደር አይችልም፡፡ ወደ ውጭ ከወጣ ግን ኮርፖሬሽኑ የሥራ አፈፃፀማቸውን ውጤት መዝኖ ቅድሚያ ይሠጣቸዋል፡

15.3 ክፍት የሥራ ቦታ መኖሩ በኮርፖሬሽኑ ዋና መ/ቤት፣በቅርንጫፎች እና በፕሮጀክት ጽ/ቤቶች ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ይገለፃል፡፡ የማስታወቂያው ይዘት በንዑስ አንቀፅ 6.31 በተገለፀው መሰረት ይሆናል፡

15.4 በክፍት የሥራ ቦታው ለማመልከት የሚፈልጉ ሁሉ ማስታወቂያው ከወጣበት እስከ 10 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ማመልከቻቸውን ለኮርፖሬሽኑ ሰው ኃብት ልማት ዘርፍ ወይም ዘርፉ ለሚወክለው ክፍል ያቀርባሉ፡

15.5 ከኮርፖሬሽኑ ሠራተኞች መካከል ተወዳድሮ ዕድገት የተሰጠው ሠራተኛ የሙከራ ጊዜ አይኖረውም፡

15.6 ዕድገት ያገኘው ሠራተኛ ተተኪ በመጥፋቱም ሆነ በሌላ ምክንያት ከ 3 (ሶስት ወር) በላይ በቀድሞ ስራው ላይ እንዲቆይ አይደረግም፡ ሆኖም ግን አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ እንደአስፈላጊነቱ ሊራዘም ይችላል፡፡

15.7 በመዋቅሩ ላይ የሥራ መደቡ የሚጠይቀውን ዝቅተኛ የትምህርት ዝግጅት አሟልቶ የተገኘ ሠራተኛ ለውድድር ሲቀርብ ያለውን ቀጥተኛ ያልሆነ ተዛማጅ የሥራ ልምድ አጥፎ ይይዛል፡፡

15.8 ለደረጃ ዕድገት የመጀመሪያ ዲግሪ ለሚጠይቁ የሥራ መደቦች በቅድሚያ የተጠየቀውን ዝቅተኛ የትምህርት መስፈርት ማሟላት ይኖርባቸዋል፡፡ የመጀመሪያ ዲግሪ ለሚጠይቁ የሥራ መደቦች የመጀመሪያ ዲግሪ ይዞ ለተገኘ አመልካች ከዲግሪ በፊት በዲፕሎማ የተገኘ ቀጥተኛ ተዛማጅ የሆነ የሥራ ልምድ በ50% እየተሰላ የሚያዝ ይሆናል፡፡ ከዲፕሎማ በታች ባለ የትምህርት ዝግጅት የተገኘ የሥራ ልምድ በዚህ ውድድር አይያዝም፡፡

15.9 በደረጀ ዕድገት የተጠየቀው ዝቅተኛ የትምህርት መስፈርት ዲፕሎማ ከሆነ ከዲፕሎማ በፊት 10/12ኛ ትምህርት አጠናቆ የተገኘ ከሥራው ጋር ቀጥተኛ ተዛማጅ የሆነ የሥራ ልምድ በ50% እየተሰላ የሚያዝ ይሆናል፡፡

### ስለ ደረጃ ዕድገት ኮሚቴ መቋቋም

15.10 ኮርፖሬሽኑ የሠራተኞችን ዕድገት የሚያይ የደረጃ ዕድገት ኮሚቴ ያቋቁማል፡

15.11 በደረጀ ዕድገት ኮሚቴ ውስጥ ሠራተኛ ማህበሩ አንድ በኮርፖሬሽኑ እና አንድ በባቡር ትራንዝት አገልግሎት ፅ/ቤት ተወካይ ይኖሩታል፡

### የመረጃ አቀራረብና የምርጫ ውጤት

15.12 ኮርፖሬሽኑ በተወዳዳሪዎች የቀረቡትን ማመልከቻዎችንና በግል ማህደር የሚገኙ መረጃዎችን አጠናቅሮ ለዕድገት ኮሚቴ ያቀርባል፡

15.13 የዕድገት ኮሚቴ የቀረበለትን መረጃ ከማህደር ጋር በማገናዘብ በሚገባ ከገመገመ በኋላ አወዳድሮ የዕድገት ውሳኔ ሃሳብ ለዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም ለሚወክለው ኃላፊ ያቀርባል፡

15.14 የዕድገት ውጤት ውሳኔ በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ይለጠፋል፡ ስለ አፈፃፀሙ ቅሬታ ያለው ተወዳዳሪ ካለ በኮርፖሬሽኑ የቅሬታ ማስተናገጃ መሠረት ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡

### የዕድገት መወዳደሪያ ነጥቦች

15.15 የትምህርት ዝግጅቱ እና የሚያድግበት የሥራ መደብ ግንኙነት፡ በሚያድግበት የራ መደብ ያለው የሥራ ልምድና ተሞክሮ፡ የማህደር ጥራት፡ ሠራተኛው በነበረበት የሥራ መደብ ያለው የሥራ አፈፃፀም ታይቶ ይሆናል፡፡ ሆኖም ከላይ በተጠቀሰው መስፈርት ተመሳሳይ ውጤት ያመጡ ተወዳዳሪዎች ለሴቶች እና ለአካል ጉዳተኞች ቅድሚያ በመስጠት በኮርፖሬሽኑ ባላቸው ቆይታ ይለያሉ እንዲሁም ለሥራ መደቡ በቂ ችሎታ ያለው መሆኑ በፅሁፍ ወይም በተግባር ወይም በቃል ፈተና ሊመዘን ይችላል፡፡ ዝርዝር ነጥብ አሰጣጡና አፈፃፀሙ በአስተዳደር መመሪያ መሠረት ይሆናል፡፡

15.16 አንድ ሠራተኛ ዕድገት ካገኘ በኋላ ለሚቀጥለው ሌላ ዕድገት ሊወዳደር የሚችለው ዕድገት ካገኘ አንድ ዓመት ከሞላው በኋላ ነው፡፡ ሆኖም ቀደም ብሎ በተካፈለው የዕድገት ውድድር ዕድገት ካላገኘ መወዳደር ይችላል፣

**ቅጥር**

15.17 በኮርፖሬሽኑ ውስጥ ክፍት የሥራ መደብ ካለ ለውስጥ ሠራተኞች ቅድሚያ በመስጠት በዚህ ንውስ አንቀጽ 15.3 እና በአንቀጽ 15.1 መሠረት ተወዳድሮ ለቦታው ተፈላጊው መስፈርት የሚያሟላ ሠራተኛ አለመገኘቱ ከተረጋገጠ የአዲስ ሠራተኛ ቅጥር ይፈፀማል፣ ሆኖም ግን ክፍት የሥራ መደቡ ለረጅም ጊዜ ሠራተኛ ሳይመደብበት መቆየቱ የሥራ እንቅፋትና አደጋ የሚፈጥር መሆኑ ከታመነበት የውስጥና የውጭ ማስታወቂያ ወጥቶ እንደአስፈላጊነቱ በእድገት ወይም በቅጥር እንዲሟላ ሊደረግ ይችላል፡፡

**ተጠባባቂ ምደባ እና ውክልና መስጠት**

15.18 በመደቡ ላይ በቂ ችሎታ ያላቸው ነገር ግን በቦታው ላይ ለማደግ አንድ አመት/1/ እና ከዚያ በታች የቀራቸውን ሠራተኞች በተጠባባቂነት መመደብ ይቻላል፡፡

15.19 በተጠባባቂነት ተመድቦ የሚያገለግል ሠራተኛ የሥራና የክፍያ መደቡ በተጠባባቂነት ከተመደበበት በፊት በያዘው ደረጃ ይሆናል። ነገር ግን ከአንድ/1/ዓመት በላይ በተጠባባቂነት መመደብ አይችልም፡፡

15.20 በተጠባባቂነት ተመድቦ በከፍተኛ ደረጃ የሚያገለግል ሠራተኛ የሥራና የክፍያ መደቡ በተጠባባቂነት ከተመደበበት በፊት በያዘው ደረጃ ይሆናል። በተጠባባቂነት ከአንድ ወር በላይ የሠራ ሠራተኛ ለቦታው የሚገባውን ለሥራ መደቡ የተመደበው መነሻ ደመወዝ እና በተጠባባቂው ደመወዝ መካከል ያለው ልዩነት ለመጀመሪያ አንድ ወር 1/4 ለሚቀጥሉት ሦስት ወራት 50 ፐርሰንት እና ከዚያ በኋላ ላለው ጊዜ 75 ፐርሰንት እየተሰላ የተጠባባቂነት አባል ይከፈለዋል፡፡

15.21 ውክልና በቅርብ ኃላፊው ጋር በመመካከር የሚወከል ሲሆን በተጠባባቂነት የሚመደብ ግን በዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም በም/ዋ/ሥራ አስፈፃሚ ወይም በቢዝነስ ዩኒት ማናጀር ሲፈቀድ የሚፈፀም ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 16
## ዝውውር

16.1 የዝውውር ዓላማ ሥራንና ሠራተኛን ለማገናኘት የኮርፖሬሽኑን የሥራ ውጤት ለማሻሻል ምርታማነትን ከፍ ለማድረግ እንዲሁም አስተዳደራዊ ችግርን ለመፍታት ነው፣

**ጊዜያዊ ዝውውር፣**

16.2 አንድ ሠራተኛ ከስድስት ወር የበለጠ በተዘዋወረበት ቦታ እንዲቆይ አይደረግም፡፡ ሆኖም መቆየቱ ለሥራው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ጊዜው ሊራዘም ይችላል፡፡

16.3 ነፍሰጡር ሠራተኛ የምትሠራበት ሥራ ለጤንነቷ አመቺ አለመሆኑ በሀኪም ሲረጋገጥ በአሰሪ እና ሠራተኛ አዋጁ አንቀጽ 87 ንኡስ አንቀጽ 4 መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፣

**ቋሚ ዝውውር፣**

16.4 ቋሚ ዝውውር ማለት ከስድስት ወር ለበለጠ ጊዜ የሚደረግ ዝውውር ነው፣ ኮርፖሬሽኑ በከፊል ወይም በሙሉ ባለድርሻነት ወደሚያቋቁማቸው ተቋማት ሰራተኞችን በቋሚነት ሊያዘዋውር ይችላል፡፡

**በኮርፖሬሽኑ በኩል**

16.5 የሠራተኛውን ችሎታ በይበልጥ በሚጠቅም ሥራ ላይ ለማዋል፣

16.6 አዲስ ሠራተኛ ከመቀጠሩ በፊት ያሉትን ሠራተኞች በሚገባ ለመደልደል፣

16.7 የአየር ፀባይና የመሳሰሉት ችግሮች ባሉባቸው ቦታዎች ያገለገሉ ሠራተኞችን ከችግሩ ለማውጣት፣

16.8 የአስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት፣

16.9 ኮርፖሬሽኑ በከፊል ወይም በሙሉ ባለድርሻነት ለሚያቋቁማቸው ተቋማት የሰው  ሀይልን ከውስጥ በመመደብ ወይም በማዘዋወር አስፈላጊ ሲሆን

**በሠራተኞች በኩል**

16.10 በጤና ችግር ምክንያት በሜዲካልቦርድ ወይም በኮርፖሬሽኑ የህክምና ባለሙያዎች ተደግፎ ሲቀርብ፣

16.11 በሌላ ምክንያት በኮርፖሬሽኑ በኩል ተቀባይነት አግኝቶ ሲቀርብ፣

16.12 በአስቸጋሪ የአየር ፀባይ የሚሰሩ ሠራተኞች ዝውውርን በተመለከተ ክፍት የሥራ መደብ ሲኖር፣አዲስ የሥራ መደብ ሲፈጠር ማስታወቂያ በሚወጣበት ጊዜ ቅድሚያ በአስቸጋሪ የአየር ፀባይ አካባቢ ለሚሰሩ ሠራተኞች ይሰጣል፣

16.13 አንድ ሠራተኛ ከአንድ የሥራ ቦታ ችሎታ ያላቸውና ተመሳሳይ የምርት ውጤት የሚያሳዩ ሠራተኞች ሲኖሩ ዝውውሩ በሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሠረት ይፈፀማል፡፡ **አንደኛ ደረጃ** የህክምና ችግር ያለበት፣ **በሁለተኛ ደረጃ** የቤተሰብ ችግር ያጋጠመው፣ **በሦስተኛ ደረጃ**

በቆላ አካባቢ እየሰራ ላለ ሠራተኛ ሲሆን እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ምክንያቶች እንደተጠበቁ ሆነው ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባቸው፡

ሀ. የአካል ጉዳት ያለበቸው ሠራተኞች፡
ለ. የአካል ጉዳት/የጤና እክል ያለባቸውን ልጆች የሚያሳድጉ ወንድ/ ሴት ሠራተኞች፡
ሐ. ልጆች ብቻቸውን የሚያሳድጉ ሴት ሠራተኞች
መ. ልጆች ብቻቸውን የሚያሳድጉ ወንድ ሠራተኞች
ሠ. ባለትዳር ሴቶች
ረ. ባለትዳር ወንዶች
ሰ. በብቸኝነት እናት ወይም አባታቸውን የሚጦሩ ሰራተኞች

16.14 ሠራተኛው ቋሚ ዝውውር በሚደረግበት ጊዜ በተቻለ መጠን የሠራተኛው ፍላጎት፡ዝውውሩ ያስፈለገበት ምክንያት፡የአገልግሎት ዘመንና የሌሎችም ተመሳሳይ ሁኔታዎች በጥንቃቄ መታየት ይኖርባቸዋል፡፡ ኮርፖሬሽኑ አስቸኳይ የሥራ ሁኔታ ካላጋጠመው በስተቀር አንድ ሠራተኛ በቋሚነት በትዕዛዝ እንዲዛወር ከመደረጉ በፊት በፈቃደኛነት የሚዛወሩ ሌሎች በተመሳሳይ የሥራ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሠራተኞች መኖራቸውን ለማረጋገጥ ኮርፖሬሽኑ በቅድሚያ ለአሥር ቀን የሚቆይ ማስታወቂያ አውጥቶ ሊያዛውር ይችላል፡፡

16.15 ተመሳሳይ የሥራ ችሎታ ኖሯቸው ከአንድ የሥራ ቦታ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ በመዛወር ተመሳሳይ አገልግሎት ለመስጠት የሚችሉ ሠራተኞች በሚገኙበት ክፍል ውስጥ ቀደም ሲል የዝውውር ግዳጃቸውን ያልፈፀሙ ሌሎች ሠራተኞች እያሉ የዝውውር ግዳጃቸውን የፈፀሙ ሠራተኞች እንዲዛወሩ አይገደዱም፡

16.16 በሠራተኛው ፍላጎት ካልሆነ በስተቀር አንድ ሠራተኛ ከአንድ የሥራ ቦታ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ በቋሚነት በመስሪያ ቤቱ ዝውውር ሲደረግ ተመሳሳይ የሥራ ችሎታ ያላቸውንና ተመሳሳይ የምርት ውጤት የሚያሳዩ ሠራተኞች ሲኖሩ ዝውውሩ በሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች መሠረት በቅደም ተከተል ያለመዛወር መብት ይሰጣቸዋል፡፡

ሀ. የአካል ጉዳት ያለበት ሠራተኛ፡

ለ. የአካል ጉዳት ያለባቸውን ልጆች የሚያሳድጉ ወንድ/ ሴት ሠራተኞች፡

ሐ. ልጆች ብቻቸውን የሚያሳድጉ ሴት ሠራተኞች

መ. ባለትዳር ሴቶች፡

ሠ. ባለትዳር ወንዶች፡

ረ. ደካማ እና ህመምተኛ ቤተሰብ ያላቸው ሴቶች እና ወንዶች

ሕጋዊ እውቅና ካለው የመንግስት ተቋም ማስረጃ ሲያቀርቡ፡

16.17 አንድ ሠራተኛ ከአንድ የሥራ ቦታ፣ የሥራ ክፍል ወይም የሥራ መደብ ወደ ሌላ የሥራ ቦታ፣ የሥራ ክፍል ወይም የሥራ መደብ በራሱ አነሳሽነት ዝውውር ሲጠይቅ ቢያንስ አንድ ዓመት በአንድ የሥራ ቦታ፣ የሥራ ክፍል ፣ ወይም የሥራ መደብ ማገልገል አለበት፡፡

16.18 አንድ ሠራተኛ ኮርፖሬሽኑ ሲያዛውረው ወይም ኮርፖሬሽኑ ክፍት የሥራ ማስታወቂያ አውጥቶ ሠራተኛው ተወዳድሮ ሲያልፍ ወይም ሠራተኛው በሜዲካል ቦርድ ወይም በኮርፖሬሽኑ የህክምና ባለሙያዎች በኩል መታመሙ ተረጋግጦ ዝውውር ሲፈቀድለት ወይም በሌላ ምክንያት ዝውውሩ ሲፈቀድ የዕቃ ማጓጓዣና የውሎ አበል ኮርፖሬሽኑ ይከፍለዋል፣

16.19 ዝውውሩ ጓዝን ማንሳት የሚጠይቅ ሆኖ ሲገኝ በቋሚነት ለሚዛወር ሠራተኛ ቢያንሰ አንድ ወር ቀደም ብሎ የዝውውር ትዕዛዝ እንዲደርሰው ይደረጋል፡፡ በትዕዛዙም ላይ የዝውውሩ ዓይነት፣ ሠራተኛው የተዛወረበት ቦታ፣ የተዛወረበት ምክንያት በተዛወረበት ቦታ የሚከፈለው ደመወዝ፣ አበልና ሌሎችም ጥቅሞች በዚህ ሕብረት ስምምነት መሠረት ተዘርዝረው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በፔሮል መተከል ይኖርባቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ አስቸኳይ የሆነ ጊዜያዊ የዝውውር ሁኔታ በሚያጋጥምበት ጊዜ ኮርፖሬሽኑ የተጠቀሰውን የጽሑፍ ትዕዛዝ ሳይሰጥ ሠራተኛው ከተዛወረበት ጊዜ ጀምሮ ከሁለት ሣምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የጊዜያዊ ዝውውር ትዕዛዝ ተዘጋጅቶ እንዲደርሰው ያደርጋል፡፡

16.20 ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ኮርፖሬሽኑ አዛውሮ ማሰራት የሚችል ሲሆን ለሚዛወሩ ሠራተኞች አስፈላጊውን የመጓጓዣ ወጪ ለቤተሰቡ እና የዕቃ መጓጓዣ ይከፍላል፡፡

16.21 በአስቸጋሪ የአየር ፀባይ አካባቢ የሚሰሩ ሰራተኞች ላይ ሰለሚፈፀም የዝውውር ሁኔታ

ሀ. በመንግስት መመሪያ መሰረት አንደኛ ደረጃ በአስቸጋሪ የአየር ፀባይ በዝውውር የተመደቡ ሰራተኞች በጽሑፍ ካላረጋገጡ በስተቀር በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ባለው ክፍት ቦታ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ይዛወራሉ፡፡ዝውውሩ ሲደረግ የመጓጓዣ ወጪና በጉዞ ላይ ለሚቆይበት ጊዜ የውሎ አበል ኮርፖሬሽኑ ይከፍላል፡፡

ለ. ከላይ በተጠቀሰው መሠረት በሁለተኛ ደረጃ አስቸጋሪ የአየር ፀባይ በዝውውር የተመደቡ ሰራተኞች ፈቃደኝነታቸውን በጽሑፍ ካላረጋገጡ በስተቀር በ3 ዓመት ጊዜ ውስጥ ክፍት ቦታ ቅድሚያ ተሰጥቶ ይዛወራሉ፡፡ዝውውሩ ሲደረግ የመጓጓዣ ወጪና በጉዞ ላይ ለሚቆይበት ጊዜ የውሎ አበል ኮርፖሬሽኑ ይከፍላል፡፡

## አንቀጽ 17
## ልዩ ልዩ ፈቃድ

### የዓመት ፈቃድ

17.1 ሁሉም ቋሚ እና ጊዜያዊ ሠራተኞች ደመወዝ እየተከፈላቸው የዓመት ዕረፍት ፈቃድ

ያገኛሉ፣

17.2 የዓመት ዕረፍት ፈቃድ መከፋፈል ወይም ማስተላለፍ አይፈቀድም፡፡ ሆኖም አስቸኳይ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ብቻ የዓመት ዕረፍት ፈቃድ በአዋጅ ቁጥር 377/96 በአንቀጽ 79 መሠረት ይፈፀማል፣

17.3 የዓመት እረፍት ፈቃድ ከሁለት ዓመት በላይ ሊተላለፍ አይችልም፡፡

17.4 አንድ ሠራተኛ በዓመት ዕረፍት ፈቃድ ላይ እንዳለች ብትወልድ ያልተጠቀመችበት የዓመት ዕረፍት ፈቃዷ የወሊድ ፈቃዷ እንዳለቀ ትጠቀምበታለች፡፡

17.5 አንድ ሠራተኛ በዓመት ዕረፍት ፈቃድ ላይ እንዳለ ተኝቶ ለመታከም ሆስፒታል ከገባ በህመም ፈቃድ ላይ እንዳለ ይቆጠራል፡፡ በህመም ፈቃደ ላይ ያሳለፋቸው ቀናት ከዓመት ዕረፍት ፈቃዱ ላይ አይቀነስበትም፡፡ ቀሪውን ፈቃድ የህመም ፈቃዱ ካበቃ በኋላ ይጠቀምበታል፣

17.6 አንድ ሠራተኛ ከኮርፖሬሽኑ ጋር የነበረው የሥራ ውል በዚህ ሕብረት ስምምነት መሠረት ሲቋረጥ እስከተሰናበተበት ጊዜ ድረስ በኮርፖሬሽኑ ያልተጠቀመበት የዓመት ዕረፍት ቀናት ካላው በገንዘብ ተለውጦ ይከፈላል፣

17.7 አንድ ዓመት በኮርፖሬሽኑ ያገለገለ ሠራተኛ 14 የሥራ ቀናት የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ያገኛል፡፡ ከአንድ ዓመት በታች ያገለገለ ሠራተኛ ላገለገለበት ወራት ተካፍሎ ዕረፍት ይሰጠዋል፡፡

17.8 ራሳቸውንም ሆነ ኮርፖሬሽኑን ለመጥቀም የሚማሩትን ሠራተኞች የፈተና ፈቃድ ከሚማሩበት ት/ቤት ሕጋዊ ማስረጃ በሚያቀርቡት መሠረት ይስተናገዳሉ፣

17.9 ከአንድ ዓመት በላይ በኮርፖሬሽኑም ሆነ በሌሎች የመንግሥት መ/ቤቶች ወይም የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም የግል ድርጅቶች ያገለገለ ሠራተኛ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 17.7 ከተመለከተው ቀን በላይ ላገለገለበት ለእያንዳንዱ ተጨማሪ አንድ አመት አንድ ቀን እየታከለበት የዓመት ዕረፍት ፈቃዱን ያገኛል፣

**የህመም ፈቃድ**

17.10 የሙከራ ጊዜውን የጨረሰ ማንኛውም ሠራተኛ ከሥራ ጋር ግንኙነት የሌለው ህመም ደርሶበት ህጋዊ ከሆነ የህክምና ተቋም ሄዶ ፈቃድ የሚያስፈልገው የህመም ፈቃድ የሚያስፈልገው ስለመሆኑ በሐኪም ከተፈቀደ የህመም ፈቃድ ከደመወዝ ጋር ይሰጠዋል፣

17.11 በንዑስ አንቀፅ 17.10 መሠረት ህመሙ ከጀመረበት ቀን አንስቶ በ12 ተከታታይ ወራት ውስጥ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

ሀ. ለመጀመሪያ 3 ወራት ጊዜ ሙሉ ደመወዝ የሚከፈልበት ፈቃድ፣

ለ. ለቀጣዩ 2 ወራት ጊዜ ግማሽ ደመወዝ የሚከፈልበት ፈቃድ፣

ሐ. ለቀጣዩ 1 ወር ያለደመወዝ ክፍያ ፈቃድ ይሰጠዋል፣

መ. ለ3 ወራት የሥራ መደቡ ክፍት ሆኖ ይጠብቀዋል፣

ሠ. የኤች.አይ. ቪ. ህመምተኞች በመንግሥት መመሪያ መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፣

17.12 ከላይ በንዑስ አንቀጽ 17.11 የተመለከተው የህመም ፈቃድ ከማለቁ በፊት የሠራተኛው የሥራ ውል ዘመን ካበቃ የህመም ፈቃዱ አብሮ ይቋረጣል፣

17.13 የህመም ፈቃድ የሚቆጠረው ሠራተኛው ፍቃድ ካገኘበት ቀን ጀምሮ የሣምንት የዕረፍት ቀናትና የህዝብ በዓላት ቀናትን ጨምሮ ፈቃዱ እስከተፈፀመበት ቀን ድረስ ያለው ጊዜ ይሆናል፣

17.14 የሙከራ ጊዜውን የጨረሰ ማንኛውም ሠራተኛ ከሥራ ጋር ግንኙነት ባለው ህመም ደርሶበት ወደ ታወቀ ሆስፒታል ወይም ጤና ጣቢያ ወይም ክሊኒክ ሄዶ የህመም ፈቃድ የሚያስፈልገው ስለመሆኑ በሃኪም ከተረጋገጠ የህመም ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡ህመሙ ከጀመረበት ቀን አንስቶ በ12 ተከታታይ ወራት ውስጥ ሙሉ ደመወዝ ይሠጠዋል፡፡ ነገር ግን በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልዳነ ጉዳቱ በሠራተኛው ምርጫ በመድህን ወይም በጉዳት ጡረታ ይሸፈናል፡፡ ሠራተኛው ከሁለት አንዱን የመምረጥ ኃላፊነት አለበት፡፡

## የወሊድ ፈቃድ

17.15 ማንኛውም ነፍሰጡር የሆነች ሠራተኛ ለምርመራ ሐኪም በሚያዘው መሠረት ደመወዝ የሚከፈልበት ፈቃድ ይሰጣታል፡፡ሆኖም ከሀኪም ቤት ስትመለስ የሀኪሙን ማስረጃ ማቅረብ ይኖርባታል፣

17.16 ነፍሰጡር የሆነች ሴት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 88 መሠረት የወሊድ ፈቃድ ታገኛለች፣

17.17 ከመውለዷ በፊት ሀኪም እንድታርፍ ካዘዘ ከክፍያ ጋር ዕረፍት ይሰጣታል፣

17.18 እወልዳለሁ ብላ ከገመተችበት ቀን በፊት መውለጃዋ ቢደርስ የ30 ተከታታይ ቀን የወሊድ ፈቃድ እንዲሁም ከወለደችበት ቀን ጀምሮ የ90 ተከታታይ ቀናት በአጠቃላይ 120 ተከታታይ ቀናት ደመወዝ የሚከፈልበት የወሊድ ፈቃድ ይሰጣታል፣

17.19 በአንቀፅ 17.18 የተቀመጠው እንደተጠበቀ ሆኖ ሠራተኛዋ መስራት እችላለሁ ካለች እና ሥራዋን መስራቱ በጤናዋ እና በፅንሱ ላይ ጉዳት (ተጽእኖ) እንደማይኖረው የሐኪም ማስረጃ ስታቀርብ የቅድመ ወሊድ ፍቃዷን ከወለደች በኃላ እንድትጠቀም ማድረግ ይቻላል፡፡

17.20 ከ5 ወር እርግዝና በኋላ ለሚደርሰው ያለ ጊዜ መውለድ ከሙሉ ደመወዝ ጋር በአንቀጽ 17.18 መሰረት የወሊድ ፈቃድ ይሰጣታል፡፡

17.21 የወሊድ ፈቃድዋን ያጠናቀቀች ሠራተኛ በተቻለ መጠን አንድ ዓመት በአዳሪ ፈረቃ (ሺፍት) እንዳትመደብ ይደረጋል፡፡

17.22 የወሊድ ፈቃዷን የጨረሰች የቢሮ ሠራተኛ እስከ 6 ወር ድረስ በየቀኑ 2፡00 ሰዓት ደመወዝ የሚከፈልበት ጡት ማጥቢያ ፈቃድ ይሠጣታል፡፡

## የአባትነት ፈቃድ

17.23 ማንኛውም ወንድ የኮርፖሬሽኑ ሠራተኛ ሚስቱ (ባለቤቱ) ለመውለድ ምጥ ሲይዛት፣ ልትወልድ ወደ ህክምና ቦታ ወይም ሆስፒታል የሚያደርስበትንና አንዳንድ ሁኔታዎችን የሚያመቻችበት ደመወዝ የሚከፈልበት አምስት /5/ ተከታታይ የሥራ ቀናት የአባትነት ፈቃድ ይሰጠዋል።

## ሕጋዊ ግዳጅ ለማስፈፀም የሚሰጥ ፈቃድ

17.24 ኮርፖሬሽኑ ለማንኛውም ሠራተኛ ከፖሊስ፣ ከፍርድ ቤት ወይም አንድን ሰው ለመጥራት ሕጋዊ ሥልጣን ካለው መ/ቤት መጥሪያ ሲደርሰው ወይም እንዲያቀርብ ሲታዘዝ ደመወዝ የሚከፈልበት ፈቃድ ይሰጠዋል፣

17.25 ሆኖም ሕጋዊ ሥልጣን ባላቸው አካላት አንድ ሠራተኛ የራሱ ጥፋት ሳይኖርበት የኮርፖሬሽኑን ህጋዊ መብት እና ጥቅም ለማስከበር ሲንቀሳቀስ በቁጥጥር ስር ሲውል ሠራተኛው በሥራ ላይ እንዳለ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡

17.26 ኮርፖሬሽኑ ሠራተኛ ለመተካት እንዲያስችለው ሠራተኛው በቅድሚያ ፈቃድ መጠየቅ አለበት፡፡ ከጊዜው አጣዳፊነት አኳያ ይህንን ለማድረግ ካልቻለ ግዳጅን ፈጽሞ ሲመለስ ማስረጃውን ማቅረብ አለበት፡፡ እንዲሁም ከሥራ ጋር በተገናኘ ምክንያት ክርክር ላይ ከሚገኙትና በመብት ጥያቄ ክስ መስርተው በቀጠሮ ለሚመላለሱት ደመወዝ የሚከፈልበት ፈቃድ ይሰጣቸዋል፣

17.27 ሆኖም ግን የመብት ጥያቄው በቅድሚያ ለአስተዳደር እና ለሠራተኛ ማህበር ቀርቦ አስፈላጊው የጽሑፍ መልስ ከተሰጠ በኋላ መልሱ አጥጋቢ ያልሆነለት ሠራተኛ

ለሚያቀርበው የመብት ክርክር ብቻ በዕለት ቀጠሮው ከደመወዝ ጋር ፈቃድ ያገኛል፡፡ ከኮርፖሬሽኑ ጋር ግንኙነት በሌለው ጉዳይ በፍ/ቤት ወይም በፖሊስ ጣቢያ ለሚመላለስ ሠራተኛ ለዚሁ ዓላማ ለሚያጠፋው ጊዜ ብቻ ፈቃድ ይሰጣል፡

17.28 ማንኛውም ሠራተኛ ከሥራው ጋር በተገናኘ የኮርፖሬሽኑን ንብረትና ህልውና ለማስጠበቅ ባለበት ኃላፊነት ምክንያት በሚደርስ ጉዳት ድርጊቱ ሕግን ያልጣሰ ከሆነና ያለአግባብ ተከሶ በፍርድ ውሳኔ ከተሰጠ በቁጥጥር ስር እያለ ሙሉ ደመወዝ እና ጥቅማጥቅም ይከፈለዋል፡፡ እስራቱን ሲጨርስ ወደ ሥራ ገበታው ይመለሳል፡

17.29 ማንኛውም ያለደመወዝ የሚሰጥ ፍቃድን መፍቀድ የሚችለው የኮርፖሬሽኑ ዋና ስራ አስፈፃሚ፡ የቢዝነስ ዩኒት ሥራ አስኪያጅ ወይም በሚወክሏቸው የሥራ ኃላፊ ነው፡፡ ዋና ሥራ አስፈፃሚው፡ ሥራ አስኪያጁ ወይም የሚወክሏቸው የሥራ ኃላፊ በቀረበው ጥያቄ ላይ በሶስት የሥራ ቀናት ውስጥ ምላሽ ይሰጣል፡፡

## የጋብቻ ፈቃድ

17.30 አንድ የኮርፖሬሽን ሠራተኛ የጋብቻ ሥነ-ስርዓት ለመፈፀም ፈቃድ ከጠየቀ አምስት ተከታታይ የሥራ ቀናት የጋብቻ ፈቃድ ከደመወዝ ጋር ይሰጠዋል፡

## የሀዘን ፈቃድ እና ተጨማሪ ድጋፎች

17.31 የአንድ ሠራተኛ ባል(ሚስት)፡ ልጆች፡ የሠራተኛውና የትዳር ጓደኛው እናት፡ አባት ከሞቱበት ቀን ጀምሮ 5 ተከታታይ ቀናት ፈቃድ ከደመወዝ ጋር፡ አያት፡ ወንድም፡ እህት ከሞቱበት ቀን ጀምሮ እንዲሁም ከቤቱ አስከሬን ከወጣ 4 ቀን ፈቃድ ከደመወዝ ጋር ይሰጠዋል፡፡ በተጨማሪም ከሠራተኛው ቤት አስከሬን ከወጣ እና የቀብር ሥነ-ስርዓቱም የሚፈፀመው በሚሰራበት የሥራ አካባቢ ከሆነ ለቀብር ሥነ-ሥርዓቱ ማስፈፀሚያ አቅም በፈቀደ መጠን አንድ መኪና ከነዳጅና ከሹፌር ጋር ኮርፖሬሽኑ ይመድብለታል፡

17.32 አንድ የኮርፖሬሽኑ ሠራተኛ ቢሞት በኮርፖሬሽኑ ውስጥ ከሚገኙ የሥራ ክፍሎች የተውጣጡ ሠራተኞች ሥራን በማይበድል ሁኔታ ለቀብሩ ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም ከደመወዝ ጋር ፈቃድ ይሰጣቸዋል፡ኮርፖሬሽኑ ለቀብር ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም ለሠራተኞች ተሽከርካሪ ያዘጋጃል፡ ሠራተኛው የሞተበት ወር የተጣራ ደመወዝ ለቤተሰቡ ይከፈላል፡፡

17.33 አንድ የኮርፖሬሽኑ ሠራተኛ ቢሞት ለሚች ቤተሰብ ኮርፖሬሽኑ 6,000.00 (ስድስት ሺ. ብር) ለቀብር ማስፈፀሚያ ይሰጣል፡፡ እንዲሁም ኮርፖሬሽኑ ካሉት ተሽከርካሪዎች ወይም በኪራይ ለአስከሬን ማጓጓዣ መኪናና አበል ይቀርባል፡፡ ተሽከርካሪ ከሌለው ይከራያል፡፡

17.34 በንዑስ አንቀጽ 17.33 የተጠቀሰው ገንዘብ የህክምናና የመድሃኒት ወጪን አይጨምርም ወይም በመድህን ውል ከተፈቀደ ክፍያ፡ ከስራ ስንብት ክፍያ ወይም ለሚች በሕግ ከተፈቀደለት ክፍያ ውስጥ አይካተትም፡

17.35 በዋናው መ/ቤት እንዲሁም በሥራ ምክንያት በጉዞ ላይ እያለና ለተወሰነ ጊዜ መስክ ላይ የተመደበ ሠራተኛ የሞት አደጋ ሲደርስ ኮርፖሬሽኑ አስከሬኑን በሚቀበርበት ቦታ በኮርፖሬሽኑ ወጭ ያጓጉዛል፡፡

## አንቀጽ 18

## የሥራ ሰዓት ዕረፍት

18.1 በሥራ ላይ ከተመደቡ ሠራተኞች በስተቀር ማንኛውም ሠራተኛ በሥራው መካከል ሰውነትን ለማዝናናት ከ4፡15 እስከ 4:30 ጧት ከሰዓት በኋላ 9፡15 እስከ 9:30 ከሰዓት በኋላ ዕረፍት ይሰጠዋል፡፡ ይህ ዕረፍት እንደመደበኛ የሥራ ሰዓት ይቆጠራል፡

18.2 በፕሮጀክት ላይ የተመደቡ ሠራተኞች እንደአየሩ ሁኔታ የዕረፍት ሰዓቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በአመቺ ሁኔታ ይሰጣል፡

18.3 በፕሮጀክት ለሚሰሩ ሠራተኞች በሥራ ጊዜያቸው 1 ሰዓት የምሣ ዕረፍት ይሰጣል፡

## አንቀጽ 19

## የሕዝብ በዓላት

19.1 ሠራተኛው ደመወዝ የሚከፈልባቸው የህዝብ በዓላት ቀናትን በዓመት ውስጥ ለማክበር መብት አለው፡፡ ነገር ግን የሥራው ልዩ ባህርይ እንዲሰራ ቢያስገድደው የበዓል ቀን ክፍያ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ መሠረት ይከፈለዋል፡፡

## አንቀጽ 20

## ትምህርትና ሥልጠና

20.1 ኮርፖሬሽኑ አቅም በፈቀደ መጠን የሠራተኞቹን ክህሎት ለማሳደግ እና የሥራ ተነሳሽነቱን እንዲጨምር ሠራተኞች እንዲማሩ ያበረታታል፡፡ ለአፈፃፀሙም የትምህርትና የሥልጠና ኮሚቴ ተዋቅሮ ከዚህ በታች በቀረበው ዝርዝር መሠረት ይፈፀማል፡፡ ሆኖም ግን ኮርፖሬሽኑ

የትምህርትና ስልጠና መመሪያና ፖሊሲ ፀድቆ ተግባራዊ ሲያደረግ በትምህርትና ሥልጠና መመሪያ መሠረት ይፈፀማል፡፡

20.2 ኮርፖሬሽኑ በራሱ ፍላጎት እና ዕቅድ መሠረት ለሚሰጠው የትምህርት ዕድል የተማሪውን ሙሉ ወጪ ይሸፍናል፣

20.3 ሠራተኛው ከሥራ ሰዓት ውጭ ራሱን ለማሻሻል በራሱ ፍላጎት እና ከስራው ጋር ቀጥተኛ ተያያዥነት ያለው ሥራን በማይበድል ሁኔታ ትምህርት እንዲማር ጠይቆ የተፈቀደለት ሠራተኛ ኮርፖሬሽኑ ሙሉ የትምህርት ወጪውን (100%) ይሸፍናል፣

20.4 ሠራተኛው በትርፍ ጊዜው እና ፍላጎት በወቅቱ ከተመደበበት ሥራ ጋር ተያያዥነት የሌለው ነገር ግን ለኮርፖሬሽኑ ጠቀሜታ ሊያስገኝ የሚችል ትምህርት እንዲማር ጠይቆ ሲፈቀድለት እና ትምህርቱን የሚማረው ሥራን በማይበድል ሁኔታ ሲሆን ኮርፖሬሽኑ 25% የትምህርት ወጪውን ይሸፍናል፣

20.5 የትምህርት ክፍያ ወጪው ሠራተኛው ፈተና ማለፉ ሲረጋገጥ በሚያቀርበው ህጋዊ ደረሰኝ መሠረት ከላይ በተጠቀሰው ድርሻ መሠረት ይወራረድለታል፣

20.6 ኮርፖሬሽኑ በራሱ ፍላጎት እና ዕቅድ መሠረት ለሚሰጠው የሥልጠና ዕድል የሥልጠናውን ሙሉ ወጪ ይሸፍናል፣

20.7 ሠራተኛው ከሥራ ሰዓት ውጭ ራሱን ለማሻሻል በራሱ ፍላጎት እና ከስራው ጋር ተያያዥነት ያለው ሥራን በማይበድል ሁኔታ በሃገር ውስጥ ሥልጠና እንዲሰለጥን ጠይቆ የተፈቀደለት ሠራተኛ ኮርፖሬሽኑ ሙሉ የሥልጠና ወጪውን (100%) ይሸፍናል፡፡ ሠራተኛውም ከስልጠናው ያገኘውን የስልጠና ቁሶች፣ ሙያ እና ክህሎት ሙሉ ለሙሉ ለኮርፖሬሽኑ ጥቅም ያውላል፡፡ ሠራተኛው ስልጠናውን ሲያጠናቅቅ የተሟላ ሪፖርት ለሰራ ክፍሉ ያቀርባል፡፡ ሠራተኛው ለስልጠና ያወጣውን ወጪ የሚያሳይ ደረሰኝ እና የስልጠና ምስክር ወረቀት ያቀርባል፤በቀረበው ደረሰኝ እና ምስክር ወረቀት መሰረት ወጪው ይወራረዳል፡፡

20.8 ሠራተኛው በትርፍ ጊዜው እና ፍላጎት በወቅቱ ከተመደበበት ሥራ ጋር ተያያዥነት የሌለው ነገር ግን ለኮርፖሬሽኑ ጠቀሜታ ሊያስገኝ የሚችል በሃገር ውስጥ ሥልጠና እንዲሠለጥን ከጠየቀ ሥራን በማይበድል ሁኔታ መሆኑ ሲረጋገጥ እና ሲፈቀድለት ኮርፖሬሽኑ 25% የሥልጠና ወጪውን ይሸፍናል፡፡ሠራተኛውም ከስልጠናው ያገኘውን የስልጠና ቁሶች፣ ሙያ እና ክህሎት ሙሉ ለሙሉ ለኮርፖሬሽኑ ጥቅም ያውላል፡፡ ሠራተኛው ስልጠናውን ሲያጠናቅቅ የተሟላ ሪፖርት ለሰራ ክፍሉ ያቀርባል፡፡ ሠራተኛው ለስልጠና ያወጣውን ወጪ የሚያሳይ ደረሰኝ እና የስልጠና ምስክር ወረቀት ያቀርባል፤በቀረበው ደረሰኝ እና ምስክር ወረቀት መሰረት ወጪው ይወራረዳል፡፡

20.9 የሥልጠና ክፍያ ወጪው ሠራተኛው በሚያቀርበው ህጋዊ ደረሰኝ መሠረት ይወራረድለታል፣

20.10 ሠልጣኙ ወይም ተማሪው ኮርፖሬሽኑ ከፍሎ አንድ ዓመት እና ከዚያ በላይ ስልጠና ወጭ ሀገር ልኮ ላሰለጠነበት ወይም አንድ ዓመት እና ከዚያ በላይ በአገር ውስጥ/ውጭ ሀገር ልኮ ላስተማረበት እጥፍ አገልግሎት ይሰጣል፡፡ ይህም ይህንን ለማስፈፀም የውል ግዴታ ይገባል ፡፡ ቀደም ሲል የተገለፀው የአገልግሎት ጊዜ እንደተጠበቀ ሆኖ እንደ ስልጠናውና ትምህርት ዓይነትና ወጪ መጠን የአገልግሎት ግዴታ ጊዜው ሊጨምር ይችላል፡፡

20.11 ኮርፖሬሽኑ የትምህርት ዕድል የሚሰጠው በኮርፖሬሽኑ ውስጥ ቢያንስ አንድ ዓመት አገልግሎት ለሰጠ ሠራተኛ ብቻ ነው፡፡

20.12 ኮርፖሬሽኑ ትምህርቱን ለደገመ ሠራተኛ ለቅጣትና ለመመዝገቢያ እንዲሁም የትምህርት ክፍያውን አይከፍልም፡፡

20.13 ከአቅም በላይ ባልሆነ ችግር ሠራተኛው የጀመረውን ትምህርት ሳያጠናቅቅ ቢያቋርጥ ወይም ትምህርቱን አጠናቅቆ የሚፈለግበትን አገልግሎት ሳይሰጥ ቢለቅ ኮርፖሬሽኑ በትምህርት ላይ እያለ የከፈለውን ደመወዝ፣የትምህርት እና ሌሎች ወጪዎች ለኮርፖሬሽኑ ተመላሽ ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ 21

## በሥራ ላይ ስለሚደርስ አደጋ

21.1 አንድ ሠራተኛ በሥራ ላይ አደጋ ወይም ከሥራ በመነጨ ወይም ከሥራ ጋር በተገናኘ ህመም ሲደርስበት በአቅራቢያው ወዳለው ሃኪም ቤት ሄዶ እንዲታከም ያደርጋል፡፡ ለዚህም አገልግሎት ኮርፖሬሽኑ የሠርቪስ መኪና ያቀርባል፣

21.2 አንድ ሠራተኛ ከሥራ በመነጨ አደጋ ወይም ምክንያት በተመደበበት የሥራ ቦታ ወይም ምድብ ሥራ ለመስራት የማይችል ለመሆኑ በሀኪሞች ቦርድ ሲረጋገጥ ኮርፖሬሽኑ ለአካሉ ተስማሚ በሆነ ቦታና ተመጣጣኝ ደረጃ ካለ ተመድቦ እንዲሰራ ያደርጋል፡፡ ይህም ሆኖ ሠራተኛው መስራት ካልቻለ በዚህ ሕብረት ስምምነት አንቀፅ 26 መሠረት ይስተናገዳል፣

21.3 ሠራተኛው ከሥራ ጋር በተገናኘ አደጋ ምክንያት ከመደበኛ ሥራ ቦታው በሀገር ውስጥ ወደ ማናቸውም ከተማ ሄዶ እንዲታከም ሀኪም በማዘዙ ሠራተኛው እንዲያወጣ የሚገደደውን የጉዞ አበልና የህክምና ወጪ ኮርፖሬሽኑ ይሸፍናል፣

21.4 ለአንድ ሠራተኛ ኮርፖሬሽኑ ከመድህን ድርጅት ጋር የ24 ሰዓት የአደጋ እና የህይወት የመድህን ሽፋን ይገባለታል፣

## አንቀጽ 22

## ከሥራ ጋር ግንኙነት ለሌላቸው ህመሞች የሚደረግ የሕክምና ወጪ

22.1 ከሥራ ጋር ግንኙነት የሌላቸው ህመሞች ሠራተኛው ሲታመም ለመታከም እንዲችል ኮርፖሬሽኑ ለአንድ ሠራተኛ በጥቅል እስከ ብር 10,000.00 (አስር ሺህ ብር) ድረስ የህክምና ወጪ ሊሸፍን የሚችል የመድን ዋስትና ሽፋን ኮርፖሬሽኑ ከመረጠው መድን ድርጅት ይገባለታል፡፡

22.2 የኮርፖሬሽኑ ሠራተኛ ሲታመም በማንኛውም ሕጋዊ የህክምና ተቋም ሄዶ ሊመረመርና ሊታከም ይችላል፡፡ከሚያቀርበው ደረሰኝ ጋር የበሽታውን ዓይነትና ሁኔታ የሚገልጽ የሀኪም ወረቀት ተያይዞ ከተላከ ለምርምራና ለህክምና ያደረገው ወጪ በንዑስ አንቀጽ 22.1 መሠረት ተመላሽ ይደረግለታል፡፡

22.3 ከሥራ ሰዓት ውጭ አንድ ሠራተኛ በድንገት ቢታመም በማንኛውም ሕጋዊ የህክምና ተቋም አገልግሎት ሊያገኝ ይችላል፡፡

22.4 የተፈቀደለት የህክምና ዶክተር ወይም የጤና ባለሙያ ሠራተኛው ሌላ ሥፍራ ሄዶ ተጨማሪ የህክምና ዕርዳታ እንዲያገኝ ከተፈቀደ በሀገር ውስጥ ለሚደረግ የህክምና ወጪ ኮርፖሬሽኑ በንዑስ አንቀጽ 22.1 መሠረት ይከፍላል፡፡ ሆኖም በሀኪም ካልታዘዘ በቀር ከሚኖርበት ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ሄዶ ለሚታከም ሠራተኛ ኮርፖሬሽኑ ወጪውን አይከፍልም፡፡

22.5 አንድ ሠራተኛ በቋሚነት ከሚሰራበት ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለህክምና በሚሄድበት ጊዜ የአውሮፕላን መጓጓዣ ካለና በአውሮፕላን መጓጓዝ የግድ ከሆነ በአውሮፕላን እንዲጓጓዝ ይደረጋል ካልሆነ ግን በኮርፖሬሽኑ መኪና ወይም በህዝብ ትራንስፖርት ተጓጉዞ ወጪውን እንዲያወራርድ ይደረጋል፡፡

22.6 አንድ የኮርፖሬሽኑ ሠራተኛ ሐኪሙ በተፈቀደላቸው የህክምና ተቋም ውስጥ የሚገኝ የህክምና ባለሙያ ከላይ በተጠቀሰው መሰረት ሆስፒታል ተኝቶ እንዲታከም የታዘዘ እንደሆነ ጠቅላላ የህክምና ወጪ ኮርፖሬሽኑ በንዑስ አንቀጽ 22.1 መሰረት ይከፍላል፡፡

22.7 ለአካል ጉዳተኞች ከቴክኖሎጂ ጋር የተገናዘበ ድጋፍ ኮርፖሬሽኑ ያደርጋል፡፡

22.8 ከሥራ ጋር በተገናኘ ለሚከሰት አደጋ/ህመም የሠራተኛው የህክምና ሙሉ ወጪ በመድህን ወይም በኮርፖሬሽኑ ይሸፍናል፣

22.9 አንድ ሠራተኛ ታክሞ ሕጋዊ ደረሰኝ ካቀረበ ኮርፖሬሽኑ ለሠራተኛው ወዲያውኑ ያወጣውን ወጪ በብር ከፍሎ ኮርፖሬሽኑ ከመድኅን ያወራርዳል፡፡

## አንቀጽ 23

## የደንብ ልብሶችና የመከላከያ መጠቀሚያዎች

23.1 የደንብና የመከላከያ ልብስ እንዲሁም የመከላከያ መገልገያ ሠራተኛ ከጀንቦች ጋር

በሚኖረው የሥራ ግንኙነት የኮርፖሬሽኑ ሠራተኞች መሆኑን ለመለየት በሚያከናውነው የሥራ ፀባይ ምክንያት ሊደርስበት ከሚችለው ጉዳት ለመጠበቅና ከሥራው ፀባይ አንፃር የሚገባውን የሥራ ልብስና መከላከያ መገልገያ በመለየት ለቋሚና ለጊዜያዊ ሠራተኞች የሚሰጥ ነው፡፡

23.2. የደንብ ልብሱም በበጀት ዓመቱ እስከ 2ኛ ሩብ ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ይሰጣል፣ቀለምና

ዓርማ በኮርፖሬሽኑ ይወሰናል፡፡የጨርቅ ጥራትን በተመለከተ በዚህ ህብረት ስምምነት በተቀመጠው ወይም ኮርፖሬሽኑ በሚወስነው መሰረት ይሆናል፡፡

23.4 የደንብ ልብሶችና የመከላከያ መገልገያ የሚሰጣቸው ሠራተኞች በንጽህናና በስነ-ስርዓት የመያዝ ግዴታ፣ የሥራ ክፍሎችም የመቆጣጠር ኃላፊነት አለባቸው፣

23.5 በዚህ ሕብረት ስምምነት መሠረት የሥራ ልብስና መከላከያ የተሰጠው ሠራተኛ በሥራ ላይ በሚገኝበት ጊዜ የተሰጠውን መከላከያ የመጠቀም የደንብ ልብሱን የመልበስ ግዴታ አለበት፡፡

23.6 አንድ ሠራተኛ የተሰጠውን የደንብ ልብሶች፣ የመከላከያ መገልገያዎች ለሌላው ሰው መስጠት መሸጥ ወይም በሌላ ጥቅም መለወጥ በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡ ሰራተኞች የተሰጣቸውን የደምብ ልብስ የመልበስ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

23.7 በመከላከያ መጠቀሚያዎች፣ በደንብ ልብሶች መገልገል የሚቻለው በምድብ ሥራ ላይ ብቻ ሲሆን ከሥራ ሰዓት ውጭ መጠቀም ክልክል ነው፣

23.8 ተቆጣጣሪዎችና ኃላፊዎች ስለመከላከያ መገልገያዎች ትክክለኛ አጠቃቀምና አያያዝ ያለውንም የደህንነት አጠባበቅ መመሪያዎችና ገላጭ ስዕሎችንም በየአካባቢያቸው በሚገኙ ግልጽ ቦታዎች በትምህርት ሰጭነት እንዲገለገሉ የመለጠፍ ግዴታ አለባቸው፣

የሚሰጡት የሥራ ልብሶች መጠን አፈጻጸም ከዚህ በታች በተመለከተው ሰንጠረዥ መሰረት ይሆናል፡፡

| ተ/ቁ | የደንብ ልብስ | መግለጫ | መጠን |
|---|---|---|---|
| 1 | ለአንድ ሙሉ ደንብ ልብስ በገበር ለሚሰፋ | ፖሊስተር/ቴትረን | 4 ሜትር |
| 2 | ለአንድ ሙሉ ደንብ ልብስ እርስ በእርሱ የሚሰፋ | ፖሊስተር/ቴትረን/ካኪ | 5 ሜትር |
| 3 | ኦቨር ኮት | ካኪ | 2 ሜትር |
| 4 | ለአንድ ሙሉ ቱታ | ካኪ | 2.5 ሜትር |

**ሠንጠረዥ 2**፡ የደንብ ልብሶች ዓይነትና መጠን

23.9 ለኮርፖሬሽኑ ሠራተኞች የሚሰጡ የሥራ ልብሶች የጨርቅ ዓይነት ለኮት፣ ለሱሪ፣ ለቱታ፣ ለጃኬትና ለ 3/4ኛ ጋውን እንደስራ ፀባያው ካኪ ቴትሮን ወይም ፖሊስተር ጨርቅ ይሆናል፡፡

23.10 ሠራተኛው የተሰጠውን የሥራ ወይም የደንብ ልብስ በሥራ ላይ እያለ በጥንቃቄ ጉድለት ባልሆነ ምክንያት ሳይሆን በአሲድና በመሳሰሉት ምክንያት ከጥቅም ውጪ በሚሆንበት ጊዜ በጊዜው ለቅርብ ኃላፊው ካሳወቀ ከጥቅም ውጪ በሆነው ምትክ ኮርፖሬሽኑ ሌላ የደንብ ልብስ ይተካለታል። የበጀት አመቱን ሙሉ ላገለገለ ሠራተኛ ሙሉ የስራ ልብስ በበጀት አመቱ አጋማሽ ለሚቀጠሩ የተፈቀደው የስራ ልብስ ሁለት ከሆነ ግማሹ እንዲሰጣቸው ይደረጋል። የተፈቀደው የደንብ ልብስ አንድ ብቻ ከሆነ አንዱ ይሰጣቸዋል።

23.11 አንድ ሠራተኛ የሥራ ልብስ ሊሰጠው የሚገባው የስራ ልብስ በሚያስፈልገው የስራ መደብ ላይ እየሰራ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው።ሠራተኛው የደንብ ልብስ በተፈቀደበት የሥራ መደብ ላይ በወቅቱ እየሰራ ከሆነ ለሥራ መደቡ የተፈቀደው የሥራ ልብስ ይሰጠዋል።

23.12 በልዩ ልዩ ፈቃድ ወይም በማንኛውም ምክንያት ስድስት ወር ድረስ በሥራ ላይ ያልነበረ ሠራተኛ ለግማሽ ዓመት የሚሰጠውን የስራ ልብስ የማግኘት መብት የለውም። ዓመቱን በሙሉ በሥራ ላይ ላልተገኘ ሠራተኛም በተመሳሳይ መልኩ ተፈጻሚ ይሆናል።

23.13 ኮርፖሬሽኑ በዚህ ሕብረት ስምምነት አባሪ በተመለከቱ የሥራ ደንቦች እንደስራቸው ሁኔታ **በአባሪ 2** የተመለከቱትን የሥራ ልብሶች፣ የአደጋ መከላከያና ሌሎችም በዝርዝሩ መሠረት የተመለከቱትን መገልገያዎች ይሰጣል፣

23.14 የሥራ ልብስ በአባሪ በተዘረዘረው መሠረት ተሰፍቶ የሚሰጥ ልብስ ይሆናል። ይህንንም ኮርፖሬሽኑ አሰፍቶ ይሰጣል፣

## አንቀጽ 24

## መዝናኛና ስፖርት

24.1 ንብረትነቱ የኮርፖሬሽኑ የሆነ የተሟላ የሠራተኛ ክበብ ያደራጃል፣

24.2 ሠራተኛ በንባብ፣ በሙያና በሥነ-ልቦና አድጎ በሀገሪቱ ዕድገትና ልማት ለመሳተፍ አቅማቸውን በመገንባት ድርሻውን ለማበርከት እንዲችሉ ኮርፖሬሽኑ ቤተ መፃህፍት አደራጅቶ አገልግሎት ይሰጣል፣

24.3 ኮርፖሬሽኑ የስፖርት መዝናኛ ወጪዎች በየዓመቱ በጀት ይይዛል፣

## አንቀጽ 25

## የሳጥን(ካዝና) መጠበቂያ ክፍያ

25.1 ኮርፖሬሽኑ በየወሩ በአማካይ በገንዘብ ተቀባይና ሰብሳቢ እና በዋና ገንዘብ ያዥ በሚንቀሳቀስ በጥሬ ገንዘብ ከዚህ በታች በተዘረዘረው መሠረት የሣጥን መጠባበቂያ ይከፍላል፣

ሀ. ዋና ገንዘብ ያዥ (ገንዘብ ያዥ) ካሸር አካውንታንት በወር ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር)

ለ. ትኬት ሻጭ፣ የካንቲን ገንዘብ ያዥ፣ ትኬት አዳይ እና ገንዘብ ሠብሳቢ በወር ብር 300.00(ሶስት መቶ ብር)

25.2. ኮርፖሬሽኑ ለገንዘብ ያዥ ወይም ለገንዘብ ሰብሳቢ ወይም ለዋና ገንዘብ ያዥ እንዲከፈል የተወሰነ ወርሃዊ የመጠባበቂያ አበል ለአሥራ ሁለት ወራት በሠራተኛው ስም መጠባበቂያ ገንዘብ መልክ ይጠራቀምለታል። ከ12 ወራት በኂላ በየወሩ ለገንዘብ ያዥ ወይም ሰብሳቢ ወይም ዋና ገንዘብ ያዥ መከፈል ይጀምራል፣

25.3 ገንዘብ ያዥ ወይም ገንዘብ ሰብሳቢው ወይም ዋና ገንዘብ ያዥ ኮርፖሬሽኑ ወይም በመንግስት ኦዲተር የተረጋገጠ ጉድለት ሲገኝበት ኮርፖሬሽኑ በሠራተኛ ስም ካጠራቀመው መጠባበቂያ ገንዘብ ተቀናሽ በማድረግ ጉድለቱን ወዲያውኑ አሟልቶ ከመጠባበቂያው ገንዘብ ላይ የተቀነሰውን ሂሳብ ከገንዘብ ያዥ ወይም ከገንዘብ ሰብሳቢው ወይም ከዋና ገንዘብ ያዥ ወርሃዊ መጠባበቂያ ክፍያ ተቀናሽ በማድረግ ይከፍላል። ጉድለቱ ከተቀማጩ በላይ ከሆነ ሠራተኛው ይከፍላል፣

25.4 የአንድ ሠራተኛ የሳጥን መጠባበቂያ አበል ከነበረበት በዕድገት ወይም በዝውውር ወይም በምደባ ቦታውን ሲለቅ እስከሰራበት ጊዜ ድረስ ታስቦ ጉድለት ከሌለበት የካዝና መጠበቂያ አበሉ ይከፈለዋል፣

25.5 የሳጥን መጠበቂያ አበል የሚከፈለው ገንዘብ ያዥ ወይም ሰብሳቢው ወይም ዋና ገንዘብ ያዥ የሥራ መደብ ላይ እስካለ ድረስ ነው፣

## አንቀጽ 26

## የሥራ ውል መቋረጥ፣ የሥራ ስንብትና የካሣ ክፍያ

26.1 **የሠራተኛ የሥራ ውል የሚቋረጠው፦**

ሀ. ሠራተኛው እና ኮርፖሬሽኑ በውል ሲስማሙ፣

ለ. ሠራተኛው በገዛ ፈቃዱ ኮርፖሬሽኑን ሲለቅ፣

ሐ. ኮርፖሬሽኑ ለዘለቄታው ሲዘጋ፣

መ. ሠራተኛው ለዘለቄታው ሥራ መስራት አለመቻሉ በሀኪሞች ቦርድ ሲረጋገጥ፣

ሠ. ከባድ እና ከስራ ሊያሰናብት የሚችለውን የጥፋት ዓይነት ሲፈፅም

ረ. ሠራተኛው በሞት ሲለይ፣

ሰ. ሠራተኛው በጡረታ ሲወጣ፣

ሸ. የሠራተኛ ቅነሳ ሲደረግ፣

26.2 የሥራ ስንብትና የካሣ ክፍያ በአዋጅ ቁጥር 377/96 እና በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 494/98 መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 27

## አስተዳደራዊ የሥነ-ሥርዓት እርምጃዎች

### የሥነ ሥርዓት እርምጃ አወሳሰድ መርህ

27.1 በሌሎች ህጎችና በኮርፖሬሽኑ የተለያዩ የአሰራር መመሪያዎች፣ ማኑዋሎች የአሰራር ሥርዓቶች የተቀመጡ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ሠራተኞች የዲስፕሊን ጥፋቶች እርምጃዎች አፈፃፀምን በተመለከተ በዚህ ክፍል በተዘረዘረው መሠረት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

27.2 ኮርፖሬሽኑ በዚህ የህብረት ሥምምነት የተደነገገውን ሥነ ምግባር ወይም ሥነ ሥርዓት በሚጥስ ወይም ተግባራዊ በማያደርግ በማንኛውም ሠራተኛ ላይ ተገቢውን የዲስፕሊን እርምጃ ይወስዳል፡፡

### የሥነ ሥርዓት እርምጃ ዓላማ

27.3 በሥነ ምግባር የታነፀ አመለካከት የዳበረ የሥራ ባህል፣የሥራ ክህሎትና የመፈፀም ብቃት ያለው ሠራተኛ እንዲፈጠር ማድረግ፣ ሠራተኛው ከፈፀመው የዲስፕሊን ግድፈት ትምህርት ወስዶ ራሱን እንዲያርም ድጋፍ በመስጠትና ክትትል በማድረግ የተሻለ ለውጥ በማምጣት ብቁ እንዲሆን ማስቻል፡፡

27.4 የዲስፕሊን እርምጃ የሚወሰደው ሠራተኛውጠ ከጥፋቱ ለማረም፣ ተመሣሣይ ጥፋት እንዳይፈጽም ለማስተማር ሌሎችም ይህንኑ ተገንዝበው ኮርፖሬሽኑን ከሚጎዳ ተግባር እንዲቆጠቡ ለማድረግ፣

27.5 ሠራተኛው መብትና ግዴታውን በድጋሚ ጠንቅቆ እንዲያውቅ ለማድረግ፣

27.6 ለቀልጣፋ ስራ፣ ለምርታማነትና ለምርት ማደግ አስፈላጊ የሆነውን ዲስፕሊን ለማስከበርና ሌሎች ሠራተኞችን ለማስተማር፣ የሚወሰደውም እርምጃ ከተፈፀመው ጥፋት ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆን ለማድረግ፣

27.7 ሠራተኛውን ለማስተማርና ከጥፋት ለመመለስ፣ የኮርፖሬሽኑን የውስጥ ደንብና የአሰራር ሥርዓት ለማስከበር እና የኮርፖሬሽኑን የሥራ ባህል በመገንባት የሰራተኛውንና የኮርፖሬሽኑን መብትና ጥቅም ለማስጠበቅ ነው፡፡

## የሥነ ስርዓት እርምጃ አፈፃፀም

27.8 ኮርፖሬሽኑ ከባድ የሥነ ሥርዓት ጥሰት ጉዳዮችን የሚመለከት የሥነ ሥርዓት ኮሚቴ ያቋቁማል፣

27.9 የሥነ ሥርዓት ኮሚቴ ከሠራተኛ ማህበሩ በኩል ሁለት ተወካዮች ይኖሩታል፣

27.10 ማንኛውም ሠራተኛ በኮርፖሬሽኑ ሃብትና ንብረት ወይም በሠራተኛ ሕይወትና ደህንነት ላይ ጉዳት በማድረስ ከተጠረጠረ በፈፀመው ጥፋት ተጠያቂ ላለመሆን ተጨማሪ አደጋ የማድረስ እና መረጃ የማጥፋት ዕድል ቢኖረው ከሥራ ይታገዳል፡፡ሆኖም በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ጉዳዩ ተጣርቶ ያልቀረበ እንደሆነ በይርጋ ይታገዳል፣

27.11 ጥፋተኛ ሆኖ አለመገኘቱ ከተረጋገጠ ወደ ስራው ሲመለስ ለታገደበት ጊዜ ያልተከፈለው ደመወዝ እና ተጨማሪ የአንድ ወር ደመወዝ የሞራል ካሣ ይከፈለዋል፣

27.12 ከደመወዝና ከሥራ የታገደ ሠራተኛ ጉዳዩ ለሥነ ሥርዓት ኮሚቴ ቀርቦ ከታየ በኋላ የሥነ ሥርዓት ኮሚቴ ባደረገው ማጣራት ሠራተኛውን ጥፋተኛ ሆኖ ካገኘውና በዋና ሥራ አስፈፃሚው ከሥራ እንዲሰናበት ከተወሰነበት እና ስንብቱ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የታገደበት ጊዜ ደመወዝና ጥቅም ሁሉ አይከፈለውም፣

27.13 ከቃል ማስጠንቀቂያ በስተቀር ማንኛውም የሥነ ሥርዓት /ዲሲፕሊን/ እርምጃ የሚወሰድበት ሠራተኛ ጥፋቱ ተጠቅሶ በጽሁፍ እንዲያውቀው ይደረጋል፣

27.14 በዚህ ሕብረት ስምምነት ውስጥ ያልተጠቀሰ ጥፋት ሠራተኛው ፈጽሞ ቢገኝ እንደ ጥፋቱ ሁኔታ በዚህ ሕብረት ስምምነት መሠረት እርምጃ ይወሰድበታል፣

27.15 ሠራተኛውን ከደረጃ ዝቅ ለማድረግና ከሥራ ለማሰናበት የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጠው የኮርፖሽኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ ብቻ ነው፡፡ ሆኖም ውሳኔው ለዋና ሥራ አስፈፃሚ ከመቅረቡ በፊት የሥነ ሥርዓት /ዲሲፕሊን/ ኮሚቴ ያየውና የውሳኔ ሃሳብ የሰጠበት መሆን አለበት፣

27.16 በሥነ ሥርዓት ማስከበሪያ እርምጃ መሠረት የሚወሰን የገንዘብ /የደመወዝ/ ቅጣት ከሠራተኛው ደመወዝ ላይ በቀጥታ እየተቀነሰ ለኮርፖሬሽኑ ገቢ ይደረጋል፣

27.17 በሠራተኛው ላይ የሚወሰደው ማንኛውም የሥነ ሥርዓት እርምጃ ለሠራተኛው በጽሑፍ ይገለፅለታል፡፡ የተወሰደውን እርምጃ ማህበሩ እንዲያውቀው ይደረጋል፣

27.18 የሥነ ሥርዓት እርምጃ ከመወሰዱ በፊት ጥፋት መፈፀሙ በማስረጃ መረጋገጥ ይኖርበታል፡

27.19 በሠራተኛው ላይ የሥነ ሥርዓት እርምጃ ሲወሰድ የሠራተኛውን ጥፋት የተላለፈውን የስምምነት አንቀጽ እና የሚወሰድበትን እርምጃ ተጠቅሶ በጽሑፍ ይሰጠዋል፡፡ በግልባጩም ከግል ማህደሩ ጋር ቅጣቱን እስኪጨርስ ብቻ ይያያዛል፡፡

27.20 ቅጣቱን ከጨረሰ በኋላ የሥነ ሥርዓት እርምጃው በማስረጃነት አይጠቀስበትም፡፡

**ቀላል እና ከባድ የሥነ ሥርዓት ጥሰቶች የሚያስከትሉት ቅጣት**

27.21 የቀላል እና የከባድ የሥነ ሥርዓት /የዲሲፕሊን/ ጥፋቶች ቅጣትን በተመለከተ በሥነ ሥርዓት እርምጃ መውሰጃ ሰንጠረዡ **አባሪ** 1 ላይ በተቀመጠው መሰረት ይሆናል፡፡

**ቅጣት በግል ማህደር የሚቆይበት ጊዜ**

27.22 የቀላል የሥነ ስርዓት ቅጣቶች ለአራት ወራት በማህደሩ ላይ ይቆያል፡

27.23 የከባድ የሥነ ስርዓት ቅጣቶች ለሰባት ወራት በማህደሩ ላይ ይቆያል፡

## አንቀጽ 28

## በአገልግሎት የሚሰጥ የምስክር ወረቀት

28.1. አንድ ሠራተኛ በዚህ ሕብረት ስምምነት መሠረት በማንኛውም ሁኔታ ከሥራ ሲሰናበት የሥራ ውሉ በመቋረጡ የሚጠይቀውን የምስክር ወረቀት በአማርኛና በእንግሊዝኛ በማዘጋጀት የሚሰጠው ሲሆን ይዘቱም የሚከተሉትን ያጠቃልላል፤

28.2 የሠራተኛው ሙሉ ስም፡ የአገልግሎት ዘመን፡ የሠራባቸው የሥራ መደቦችና ቦታዎች፡ ስለሥራው ያለው ችሎታ፡ የጡረታ መዋጮ እና ሌሎች ክፍያዎች ለመከፈሉ ማረጋገጫ የተፃፈበት የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

28.3 አንድ ሠራተኛ በማንኛውም ጊዜ የሚጠይቀውን የሥራ ልምድ ወይም ሌላ የምስክር ወረቀት በአማርኛና በእንግሊዝኛ በማዘጋጀት የሚሰጠው ሲሆን ይዘቱም ከላይ በ28.2 መሠረት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 29

## የቅሬታ አቀራረብ ስነ ስረዓትና አወሳሰን

29.1 ማንኛውም የኮርፖሬሽኑ ሠራተኛ ከሥራ ውል ጋር በተያያዘ ቅሬታ ሲሰማው በየደረጃው ለሚመለከተው የሥራ ኃላፊ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡

29.2 የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ፣ የደመወዝ ቅጣት የተወሰነበት ሠራተኛ እርምጃውን ከወሰደው አካል ቀጥሎ ላለው አካል ቅሬታውን አቅርቦ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ ምላሽ ማግኘት አለበት፡፡ ሠራተኛው በውሳኔው ላይ ቅሬታ ካለው በኮርፖሬሽኑ ደረጃ የመጨረሻውን ውሳኔ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ ያገኛል፡

29.3 ከሥራ ደረጃና ደመወዝ ዝቅ የተደረገ ወይም ከሥራ የተሰናበተ ሠራተኛ እርምጃውን ከወሰደው አካል ቀጥሎ ላለው አካል ቅሬታውን አቅርቦ በሰባት ቀናት ውስጥ ምላሽ ማግኘት አለበት፡፡ ሠራተኛው በውሳኔው ላይ ቅሬታ ካለው በኮርፖሬሽኑ ደረጃ የመጨረሻውን ውሳኔ በሰባት የሥራ ቀናት ውስጥ ያገኛል፡

29.4 ሠራተኛው ከመብቶችና ጥቅሞች አጠባበቅ፣ ከሥራ አካባቢ ጤንነትና ደህንነት ሁኔታዎች ከሥራ ምደባና ደረጃ አሰጣጥ እና የሥራ ሁኔታዎችን የሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች ላይ ቅሬታውን ለሚመለከተው አካል አቅርቦ በተሰጠው ውሳኔ ቅር ከተሰኘ ውሳኔውን ከሰጠው አካል ቀጥሎ ባለው አካል አቤቱታውን አቅርቦ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ ምላሽ ማግኘት አለበት፡፡ ሠራተኛው በውሳኔው ላይ ቅሬታ ካለው በኮርፖሬሽኑ ደረጃ የመጨረሻውን ውሳኔ በአስር የስራ ቀናት ውስጥ ያገኛል፡፡

29.5 ከላይ በአንቀጽ 29 ንዑስ አንቀጽ 29.1፣29.2፣29.3 እና 29.4 የተጠቀሱት እንዳሉ ሆነው ነገር ግን ሠራተኛው በተሰጠው የመጨረሻ ውሳኔ ካልተስማማ ጉዳዩን አግባብ ላለው የውሳኔ ሰጪ አካል ማቅረብ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 30

## ምክክር

30.1 በኮርፖሬሽኑና በኮርፖሬሽኑ ሠራተኞች መካከል ግንኙነት፣ መተሳሰብ፣ ስምምነትና ፍፁም የሆነ የሥራ መግባባት እና ተነሳሽነት እንዲኖር የኮርፖሬሽኑን ግንባታ ወይም አገልግሎት በየጊዜው እያደገ እንዲሄድና እንዲሁም የኮርፖሬሽኑ ሠራተኞች የሥራ ሁኔታዎች በሕጉና በዚህ የሕብረት ስምምነት መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ ከአሠሪው ወይም ከማህበሩ አንደኛው ጥሪ ሲያቀርብ የሥራ ወቅታዊ ችግሮች መፍትሄ ለመስጠት፣ የኮርፖሬሽኑ የኢንዱስትሪ ሠላም ለማስከበርና ህልውናውን ለመታደግ ማኔጅመንቱና የሠራተኛ ማህበሩ አስፈላጊውን ምክክር በማድረግ ተገቢው ውሳኔ መስጠት ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ 31

## የመጓጓዣ አገልግሎት ስለመስጠት

31.1. የመጓጓዣ አገልግሎት በአንቀጽ 6 በንዑስ አንቀጽ 6.8 እና 6.9 መሠረት የሚሰጥ ይሆናል፡

ሀ. በአዲስ አበባ ከተማ የሠርቪስ ስምሪት መስመር የኮርፖሬሽኑ ሠርቪስ ተጠቃሚ ሠራተኞችን ብዛት በማመዛዘን ኮርፖሬሽኑና የሠራተኛው ማህበር በሚስማሙበት የስምሪት መስመር የወል/የጋራ/ የመጓጓዣ አገልግሎት ያቀርባል፡፡

ለ. ኮርፖሬሽኑ የመጓጓዣ አገልግሎት መስጠት በማይችልባቸው ቦታዎች ላይ ላሉ ሠራተኞች የመጓጓዣ አበል በወር 500.00 (አምስት መቶ ብር) ይከፍላል፡፡

ሐ. ከአዲስ አበባ ውጭ በሚገኙ የሥራ ቦታዎች ለሚሰሩ ሠራተኞች የሥራ ፀባያቸው የመጓጓዣ አገልግሎት የሚጠይቅ ከሆነ ኮርፖሬሽኑ ያቀርባል፡፡

መ. ኮርፖሬሽኑ ሰርቪስ በሚሰጥበት መስመር ላይ አገልግሎቱን አልፈልግም በብር ይቀየርልኝ ማለት በየትኛውም አግባብ ተቀባይነት የለውም፡፡

## አንቀጽ 32

## ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅም ክፍያ

32.1 ሊከሰት የሚችል አደጋ ቀድሞ እንዳይከሰት የተከላከለ/ያዳነ እንዲሁም ልዩ ፈጠራ ለፈጸመ ሠራተኛ በሚመለከተው የሥራ ክፍል ሲረጋገጥና ሲፈቀድ በሽልማት መልክ ከ5,000.00 (አምስት ሺ. ብር) እስከ 10,000.00(አስር ሺ. ብር) የሚደርስ የብር ሽልማት ይሰጣል፡፡

32.2 ለባቡር አሽከርካሪዎች (የባቡር ማስተር አስተባባሪዎች፡ የባቡር ማስተሮች) ሥራው ትእግስት፡ ትኩረት፡ የተጓዥ ደህንነት የሚጠይቅና ቀደም ብለው መግባትና ከሥራ ሰዓት ውጪ የሚከናወን ፣ የኮርፖሬሽኑን ገጽታ ግንባታ የሚታይበት ልዩ የሥራ ፀባይ በመሆኑ በየወሩ ብር 1,500.00 (አንድ ሺ አምስት መቶ) ያልተጣራ ይከፈላል፡ ሆኖም ግን በስነ-ምግባር ጉድለት፡ በተከታታይ ከ30 ቀን በላይ በሥራ ገበታው ላይ ያልተገኘ

እንዲሁም በሌሎች ምክንያቶች ባቡር የማያሽከረክር ከሆነ ሙሉ ለሙሉ ክፍያው አይመለከተውም፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ 5 ተያይዟል)

32.3 በባቡር ዘርፍ ከባቡር ተቋም ልዩ የሙያ ክህሎት ስልጠና ወስደው አስፈላጊውን ምዘና በማሟላት የብቃት ማረጋገጫ ለሚያቀርቡና ሙያቸው ከዚህ በታች ለተዘረዘሩ ባለሙያዎች ማለትም፣

- ❖ ቴክኖሎጂ አስተባባሪ፣ ለኮምፕርሂንሲቭ አስተባባሪ፣ ለOCC Dispatching Coordinators እና ለ Depot Dispatching Coordinators፣ engineering vehicle drivern እና engineering veichle coordinator/፣ የባቡር እንቅስቃሴ አሳላጮች (all dispatchers) እና የጥገና ባለሙያዎች (power supply, signaling and communication, construction, rolling stock, equipment guarantee technicians)፣የጥንቃቄና የደህንነት ባለሙያዎች፣ በየወሩ ብር 1,000.00(አንድ ሺ.ህ) ያልተጣራ ይከፈላል፡፡ ሆኖም ግን በስነምግባር ጉድለት፣ በተከታታይ ከ30 ቀን በላይ በሥራ ገበታው ላይ ያልተገኘ እንዲሁም በሌሎች ምክንያቶች ባቡር የማያሽከረክር ከሆነ ሙሉ ለሙሉ ክፍያው አይመለከተውም፣ ፡ (ዝርዝሩ በአባሪ 5 ተያይዟል)

32.4 በመደበኛነት አዲስ አበባ ውስጥ ተመድበው አገልግሎት ለሚሰጡ የሰርቪስ መኪና አሽከርካሪዎች ሠራተኞች አልፎ አልፎ ከሥራ ሰዓት ዉጪ ለኃላፊዎች ጭምር ቀደም ብሎ ወደ ሥራ ገበታቸው የሚገባ እና ከሥራ ሰዓት ውጪ አምሽተው ለሠራተኞች የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥና በትርፍ ሥራ ይስሩ ቢባል አፈፃፀሙ ውስብስብ ስለሚሆን ይህንን አገልግሎት ለሚሰጡ ሾፌሮች በየወሩ ብር 1,500.00(አንድ ሺ.ህ አምስት መቶ) ቶፕ አፕ ያልተጣራ እንዲከፈላቸው ሆኖ አከፋፈሉ የሥራ ክፍሉ በሚያቀርበው አቴንዳንስ መሠረት ይሆናል፡፡

32.5 ኮርፖሬሽኑ ለአንድ የኮርፖሬሽኑ ሠራተኛ እሱን/ሷን/ ሳይጨምር ሁለት (2) የነፃ የባቡር መጓጓዣ መታወቂያ ይሰጣል፣

## አንቀጽ 33

## የሌሊት አበል

33.1 ከምሽቱ 4:01 እስከ ንጋቱ12:00 ድረስ ለሚሠሩ ሠራተኞች የሌሊት አበል ይከፍላል፡፡

የሌሊት አበል አከፋፈል ሁኔታ እና የገንዘብ መጠን የሥራ ደረጃን፣ የሙያ ባህሪን እንዲሁም የቅጥር ሁኔታን መሠረት አድርጎ በሦስት ደረጃዎች የተከፈለ ነው፡፡ በዚሁ መሠረት በወር የሚከፈለው የሌሊት አበል እንደሚከተለው ይፈፀማል፣

33.2 **ለደረጃ አንድ** ሠራተኞች በቀን ሲያድሩ ብር 100.00 (አንድ መቶ ብር) ይከፈላል፡፡ የሚሰሩበት ቀናት ከ15 ቀን የማይበልጥ ሆኖ በአንድ ወር ውስጥ ከብር 1500.00 (አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር) አይበልጥም፡፡ ሆኖም በወሩ መጨረሻ የሠራባቸው ቀናት ከሥራ ክፍላቸው የሰዓት መቆጣጠሪያ እየቀረበ መሆን ይኖርበታል፣

33.3 **ለደረጃ ሁለት** ሠራተኞች በቀን ሲያድሩ ብር 70.00 (ሰባ ብር) ይከፈላል፡፡ የሚሰሩበት ቀናት ከ10 ቀን የማይበልጥ ሆኖ በአንድ ወር ውስጥ ከብር 700.00 (ከሰባት መቶ ብር) አይበልጥም፡፡ ሆኖም በወሩ መጨረሻ የሠራባቸው ቀናት ከሥራ ክፍላቸው የሰዓት መፈቆጣጠሪያ እየቀረበ መሆን ይኖርበታል፣

33.4 **ለደረጃ ሶስት** ሠራተኞች በቀን ሲያድሩ ብር 40.00 (አርባ ብር) ይከፈላል፡፡ የሚሰሩበት ቀናት ከ10 ቀን የማይበልጥ ሆኖ በአንድ ወር ውስጥ ከብር 400.00 (ከአራት መቶ ብር) አይበልጥም፡፡ ሆኖም በወሩ መጨረሻ የሠራባቸው ቀናት ከሥራ ክፍላቸው የሰዓት መፈቆጣጠሪያ እየቀረበ መሆን ይኖርበታል፣

33.5 በሦስቱም ደረጃዎች ከምሽቱ 2፡00 ሰዓት እስከ ምሽቱ 4፡00 ሰዓት ለሚሰሩ ሰራተኞች የተመደቡበትን ደረጃ የአዳር ክፍያ 1/3ኛ (አንድ ሦስተኛ) ብር ይከፈላቸዋል፡፡

33.6 መደበኛ ሥራቸው በሽፍት ያልሆነ በሌሊት የሥራ ሰዓት ብቻ እንዲሰሩ የተቀጠሩ ባለሙያዎች በወር ብር 700.00(ሰባት መቶ ብር) የሌሊት አበል ይከፈላቸዋል፡፡ ይህን ክፍያ የሚያገኙ ከላይ በተገለፁት ደረጃዎች ውስጥ ያልተካተቱ ናቸው፡፡

33.7 የሽፍት ሥራ ማነቃቂያ አበል የሚከፈለው ሠራተኛው  በቀን የሚገኘው የሽፍት ሥራ ክፍያ አበል በሰዓት ተካፍሎ በሥራ ላይ በቆየበት ሰዓት ብቻ ተሰልቶ ይከፈለዋል፡፡

33.8 የሌሊት አበል ክፍያ ጥያቄው ከመቅረቡ አንድ ወር በፊት የሥራ ክፍሎች የሠራተኞችን የሥራ ፕሮግራም አስቀድመው በማውጣት ለቢዝነስ ዩኒት ሥራ አስኪያጅ ቀርቦ  ፀድቆ ለሰው ኃብት እና ፋይናንስና አስተዳደር መላክ አለበት፡፡

33.9 በፈረቃ ለሚሰሩ ሰራተኞች የኮርፖሬሽኑ የስራ ክንውን የማያደናቅፍ ወይም በኮርፖሬሽኑ ላይ ተጨማሪ ወጪ የማያስከትል ከሆነ በእኩል የስራ ደረጃ ያሉ በፈረቃ የሚሰሩ ሰራተኞች ከ8 ሰዓት በፊት ለቅርብ ኃላፊው አሳውቀው የፈረቃቸውን መረሐ ግብር ሊቀያየሩ ይችላሉ፡፡

33.10 ኮርፖሬሽኑ ካለበት የስራ ጫና አንፃር እና ያልተቆራረጠና ቀጣይነት ያለው የባቡር አገልግሎት ለመስጠት ያስችል ዘንድ ለ8 ሰዓት ስራ እንዲሰራ በፈረቃ ስራ ጊዜ ለስራ የመጣ ሠራተኛ የፈረቃ ስራ ለሁለት የተከፈለ ካልሆነ በስተቀር ኮርፖሬሽኑ የ8 ሰዓት ስራ ባይሰጠውም 8 ሰዓት እንደሰራ ይታሰብለታል፡፡ ሆኖም የፈረቃው ሥራ ለሁለት በመከፈሉ ምክንያት ከስር ወደ ቤቱና ከቤት ወደ ስራው ለሚመላለስ ሠራተኛ ኮርፖሬሽኑ የመጓጓዣ አገልግሎት ይሰጠዋል፡፡

33.11 በማታ ፈረቃ ሥራ የጀመረ ሠራተኛ ሥራው ወደ ሌሊት ከቀጠለ የሚከፈለው የፈረቃ አበል ይከፈል በነበረበት የፈረቃ ጊዜ አበል መሠረት ይሆናል፡፡

33.12 በማታ ወይም በሌሊት ፈረቃ ሥራ የጀመረ ሠራተኛ ሥራው ወደ ቀን ከቀጠለ የሚከፈለው የፈረቃ ክፍያው ለሰራበት ጊዜ በሙሉ በሌሊት የፈረቃ ክፍያ ታስቦ ይከፈለዋል፡፡

33.13 በፈረቃ የትርፍ ሰዓት ሥራ ለሚሰሩ ሠራተኞች ከሰሩት የትርፍ ሰዓት በተጨማሪ ተገቢው የፈረቃ አበል ይከፈላቸዋል፡፡

| ተ.ቁ | ማብራሪያ |
|---|---|
| 1 | **<u>በደረጃ አንድ የተመደቡ የሙያ አይነቶች</u>** |
| | ለቴክኖሎጂ አስተባባሪ፣ ለኮምፕርሄንሲቭ አስተባባሪ፣ የባቡር ማስተር አስተባባሪዎች፣ ለ OCC Dispatching Coordinators እና ለ Depot Dispatching Coordinators፣ የባቡር ማስተሮች / train master, engineering vehicle driver/፣ engineering vehicle Coordinators የባቡር እንቅስቃሴ አሳላጮች (all dispatchers) እና የጥገና ባለሙያዎች (power supply, signaling and communication, construction, rolling stock, equipment guarantee technicians) ፣የጥንቃቄና የደህንነት ባለሙያዎች፣ |
| 2 | **<u>በደረጃ ሁለት የተመደቡ የሙያ አይነቶች</u>** |
| | የአይ.ሲ.ቲ ባለሙያዎች፣የኢኩፕመንት ባለሙያዎች፣ የማሽን ኦፕሬተሮች፣ የትኬት ሽያጭ ሰራተኞች፣የባቡር አስተናጋጆች(train hosts)፣ የኳሊቲ እና የአካባቢ ጥበቃ ኤክስፐርቶች፣ ለትኬት ሽያጭ አስተባባሪዎች፣ለትኬት ቁጥጥር አስተባባሪዎች፣ለሊፍት ሰራተኞች አስተባባሪዎች፣ስካሌተር ኦፕሬሽን ሠራተኛ አስተባባሪዎች፣ ለገቢ ሂሳብ ሠራተኛ አስተባባሪዎች፣ የካፍቴሪያ ሠራተኛ አስተባባሪዎች፣ ዎች ማን (Watch men) አስተባባሪዎች፣ የቀላል መኪና ሹፌሮች፣ከባድ መኪና ሹፌሮች፣ |
| 3 | **<u>በደረጃ ሦስት የተመደቡ የሙያ አይነቶች</u>** |
| | የመሳሪያ አቅራቢዎች፣ ዎች ማኖች (Watch men) ፣የሊፍትና ስካሌተር ኦፕሬተሮች፣ ትኬት አዳዮች/ለገቢ ሂሳብ ሰራተኞች፣ ፣የትኬት ተቆጣጣሪዎች፣ የካፍቴሪያ ሠራተኞች፣ የፎቶ ኮፒ ሠራተኞች፣ |

ሠንጠረዥ 3፡ የሙያ ዓይነትና ደረጃዎቻቸው

33.14 በፈረቃ ለሚሰሩ ሰራተኞች የኮርፖሬሽኑን የሥራ ክንውን የማያደናቅፍ ወይም በኮርፖሬሽኑ ላይ ተጨማሪ ወጪ የማያስከትል ከሆነ በእኩል የስራ ደረጃ ያሉ በፈረቃ የሚሰሩ ሰራተኞች የፈረቃቸውን መርሐ-ግብር ሊቀያየሩ ይችላሉ፤

33.15 በፈረቃ የትርፍ ሰዓት ሥራ ለሚሰሩ ሰራተኞች ከሰሩት የትርፍ ሰዓት በተጨማሪ ተገቢው የፈረቃ አበል ይከፈላቸዋል፤

## አንቀጽ 34

## የሥራ አስተባባሪዎች አበል

34.1 የሥራ አስተባባሪዎች በሥራቸው ሠራተኞችን ስለሚያስተባብሩና የሥራ መሪ ባህሪያለው በመሆኑ የሥራ አስተባባሪነት አበል ይከፈላቸዋል፡፡ በዚህም መሠረት በዚህ ህብረት ሥምምነት **በአባሪ** 4 በተያያዘው መሠረት እንደሚከተለው ክፍያ ይፈፀማል፤

- ሀ. በደረጃ አንድ ለተመደቡ ሠራተኞች በወር 1,000.00 (አንድ ሺ.ህ ብር) ፤
- ለ. በደረጃ ሁለት ለተመደቡ ሠራተኞች በወር ብር 800.00 (ስምንት መቶ ብር) ይከፈላል፤
- ሐ. በደረጃ ሦስት ለተመደቡ ሠራተኞች በወር ብር 300.00(ሦስት መቶ) ይከፈላል፤

34.2 በተከታታይ ከ30 ቀን እና ከዚያ በላይ በማንኛውም ምክንያት በሥራ ላይ ያልተገኘ ሠራተኛ የአስተባባሪነት አበል አያገኝም፡፡

## አንቀጽ 35

## የጽዳት መጠበቂያ

35.1 የኮርፖሬሽኑ ሠራተኞች የጽዳት መጠበቂያ በሚከተለው ዝርዝር መሠረት ይሰጣል፤

| ተ.ቁ | የዕቃው ዓይነት | ብዛት (በቁጥር) | መጠን | ጊዜ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሶፍት | 1 | 100 ግራም | በየወሩ | ለሁሉም ሠራተኛ |
| 2 | የገላ ሣሙና | 1 | 125 ግራም | በየወሩ | |
| 3 | የልብስ ሣሙና | 1 | 250 ግራም | በየወሩ | የሥራ ልብስ ለሚሰጣቸው |
| 4 | ኦሞ | 1 | 500 ግራም | በየወሩ | |

**ሠንጠረዥ 4፡** የጽዳት መጠበቂያ ዕቃዎች ዝርዝር እና መጠን

## አንቀጽ 36
## የወተት አበል

36.1 ኮርፖሬሽኑ ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት የሥራ መደቦች በየቀኑ ½ (ግማሽ) ሊትር ወተት ይሰጣል፡፡ ወተት አበል አንድ ወር ሙሉ በተለያየ ምክንያት ከስራ ገበታው ለቀረ ሠራተኛ አይከፈለውም፡፡ በዚህ ህብረት ስምምነት መሠረት ወተት ሊሰጣቸው የሚገባ ሠራተኞችን የሥራ ክፍል ኃላፊዎች በየወሩ አረጋግጠው በሚያቀርቡት ሪፖርት መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡ ክፍያውም በቀን ግማሽ ሊትር ወተት ያቀርባል ወይም በገንዘብ ቀይሮ (ብር 350.00) ይከፈላል፡

| ተ.ቁ | የሥራ መደብ ዝርዝር |
|---|---|
| 1 | Chef |
| 2 | Hot kitchen superviser |
| 3 | Fashioning chef |
| 4 | pretreatment chef |
| 5 | Enjera Gagari |
| 6 | Central kitchen superviser |
| 7 | Baresta |
| 8 | Photocopier |
| 9 | Generator Operators |

**ሠንጠረዥ 5፡** የወተት አበል የሚከፈላቸው የሥራ መደቦች ዝርዝር

## አንቀጽ 37
## ስምምነቱ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ

37.1 ይህ የሕብረት ስምምነት በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ፀድቆ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ሦስት ዓመት የፀና ይሆናል፡፡ ሆኖም አዲስ የሕብረት ስምምነት እስኪደረግ እና እስኪፀድቅ ድረስ ይህ የሕብረት ስምምነት ተፈፃሚ ይሆናል፡

## አንቀጽ 38

## የሕብረት ስምምነት ስለማሻሻል

38.1 ይህ የሕብረት ስምምነት ለማሻሻል ወይም ተጨማሪ ስምምነት ለማድረግ ባስፈለገ ጊዜ በኮርፖሬሽኑ ወይም በሠራተኛ ማህበሩ አነሳሽነት በሚደረግ ድርድርና ስምምነት ሦስት ዓመት ባይሞላውም በመካከል በከፊል ወይም ሙሉ ለሙሉ ሊሻሻል ይችላል፡፡

## አንቀጽ 39

## ስምምነት ስለመፈራረም

39.1 ይህን የሕብረት ስምምነት ተዋዋይ ወገኖች በኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን እና በኢትዮጵያ የምድር ባቡር ኮርፖሬሽን መሠረታዊ የሠራተኛ ማህበር ስም ተስማምተን በፊርማችን አጽድቀናል፣

ዶ/ር ስንታየሁ ወ/ሚካኤል
ስለ ኮርፖሬሽኑ

አቶ ዳዊት በላቸው
ስለ ማህበሩ

አባሪ 1: የሥነ

## ሥርዓት እርምጃ አወሳሰድ ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | የጥፋት አይነት | የጥፋት ደረጃ | የቅጣት እርምጃዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የመጀመሪያ ጥፋት | ሁለተኛ ጥፋት | ሦስተኛ ጥፋት | አራተኛ ጥፋት | አምስተኛ ጥፋት |
| 1 | ያለፈቃድ ወይም ያለበቂ ምክንያት በተከታታይ **ሰባት** የሥራ ቀናት ከሥራ ገበታው የቀረ፣ | ከባድ | የሥራ ስንብት | | | | |
| 2 | የለፈቃድ ወይም ያለበቂ ምክንያት በጠቅላላው በወር ውስጥ **ለአስር አራት** ከሥራ ገበታው የቀረ፣ | ከባድ | የሥራ ስንብት | | | | |
| 3 | ያለፈቃድ ወይም ያለበቂ ምክንያት በጠቅላላው በአንድ ዓመት ውስጥ ለሠላሳ የሥራ ቀናት ከሥራ ገበታው የቀረ፣ | ከባድ | የሥራ ስንብት | | | | |
| 4 | በቸልተኝነት ወይም በመደበኛ ሥራው ላይ ተገቢውን ጥንቃቄና ትኩረት ባለመስጠት ሥራ ማጓተቱ በማስረጃ ሲረጋገጥ፣ | ቀላል | የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ | የ5 ቀን ደመወዝ በሥራ ክፍሉ በኩል | የ15 ቀን ደመወዝ | የ አንድ ወር ደመወዝ | ጉዳዩ ለዲሲፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ እስከ ሥራ ስንብት |
| 5 | የኮርፖሬሽኑን ተሽከርካሪ ያለአግባብ በመንዳት ጉዳት ማድረስ በማስረጃ ሲረጋገጥ፣ | ከባድ | ለዲሲፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ የደረሰውን ጉዳት መሰረት በማድረግ እስከ 1 ወር የደመወዝ ቅጣት | ጉዳዩ ለዲሲፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ እስከ ሥራ ስንብት | | | |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 6 | ስክሮ ወይም አደንዛዥ ዕጽ ተጠቅሞ የኮርፖሬሽኑን ተሽከርካሪ መንዳት፣ ጉዳት ማድረስ በማስረጃ ሲረጋገጥ፣ | ከባድ | የሥራ ስንብት | | | | | |

| ተ.ቁ | የጥፋት አይነት | የጥፋት ደረጃ | የቅጣት እርምጃዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የመጀመሪያ ጥፋት | ሁለተኛ ጥፋት | ሦስተኛ ጥፋት | አራተኛ ጥፋት | አምስተኛ ጥፋት |
| 7 | የኮርፖሬሽኑን ተሽከርካሪ ላልተፈቀደ ተግባር ማዋል በማስረጃ ሲረጋገጥ፣ | ከባድ | ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ እንደጉዳዩ ክብደትና ቅለት ከጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እስከ ሥራ ስንብት | | | | |
| 8 | በሥራ ቦታ ላይ የሚያሰክር መጠጥ መጠጣት፣ ጫት መቃም፣ አደንዛዥ ዕፅ መጠቀም፣ በኮርፖሬት ቅጥር ግቢ ይዞ መገኘት በማስረጃ ሲረጋገጥ፣ | ከባድ | ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይበማድረግ የሥራ ስንብት | | | | |
| 9 | መለያ ምልክት /ባጅ/ ያላደረገ፣ ፡ የደንብ ልብስ በሥራ ቦታ ላይ አለመልበስ | ቀላል | የቃል ማስጠንቀቂያ በጽሑፍ በሥራ ክፍሉ በኩል ይሰጠዋል በማህደሩ አይያያዝም | የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በጽሑፍ በሥራ ክፍሉ በኩል ይሰጠዋል በማህደሩም ይታሰራል | የ5 ቀን ደመወዝ በሥራ ክፍሉ በኩል/በሰው ሃብት ልማት ዘርፍ/መምሪያ | የ15 ቀን ደመወዝ በሥራ ክፍሉ በኩል/በሰው ሃብት ልማት ዘርፍ/መምሪያ | ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይበማድረግ እስከ ሥራ ስንብት |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 10 | የመከላከያ መጠቀሚያ አለመጠቀም | ከባድ | የ3 ቀን ደመወዝ ቅጣት በሥራ ክፍሉ በኩል/በሰው ሃብት ልማት ዘርፍ/መምሪያ | የ10ቀን ደመወዝ ቅጣት በሥራ ክፍሉ በኩል/በሰው ሃብት ልማት ዘርፍ/መምሪያ | የ1 ወር ደመወዝ ቅጣት በሥራ ክፍሉ በኩል/በሰው ሃብት ልማት ዘርፍ/መምሪያ | ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ እስከ ሥራ ስንብት | |
| 11 | የመከላከያ መጠቀሚያና የደንብ ልብስ የሸጠ፣ ለሌላ ሰው ያስተላለፈ በማስረጃ ሲረጋገጥ፣ | ቀላል | የ5 ቀን ደመወዝ በሥራ ክፍሉ በኩል በሚሰጥ ውሳኔ ይቆረጣል፣ | የ15 ቀን ደመወዝ በሥራ ክፍሉ በኩል/በሰው ሃብት ልማት ዘርፍ/መምሪያ | ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ እስከ ሥራ ስንብት | | |
| 12 | በኮርፖሬሽኑ ንብረት ወይም ቅጥር ግቢን ሕገ ወጥ ለሆነ ተግባር የተጠቀመ ወይም ሌላ ወገን እንዲጠቀምበት ያደረገ በማስረጃ ሲረጋገጥ፣ | ከባድ | ለዲስፕሊን ኮሚቴ በማቅረብ የሥራ ስንብት | | | | |

| ተ.ቁ | የጥፋት አይነት | የጥፋት ደረጃ | የቅጣት እርምጃዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የመጀመሪያ ጥፋት | ሁለተኛ ጥፋት | ሦስተኛ ጥፋት | አራተኛ ጥፋት | አምስተኛ ጥፋት |
| 13 | ተረኛ ሆኖ በተመደበበት የሥራ ገበታ ላይ ሳያሳውቅ ወይም ሳያስፈቅድ አለመገኘት ፣ወይም ስራ ከገቡ በኋላ ሳያስፈቅድ ወይም ለቅርብ አለቃ ሳያሳውቁ ከስራ ገበታ ላይ መለየት | ቀላል | የዕሁፍ ማስጠንቀቂያ በሥራ ክፍሉ በኩል በሚሰጥ ውሳኔ፣ | የ5 ቀን ደመወዝ ቅጣት በሥራ ክፍሉ በኩል | የ15 ቀን ደመወዝ ቅጣት በሥራ ክፍሉ በኩል | የ1 ወር ደመወዝ ቅጣት በሥራ ክፍሉ በኩል | ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ እስከ ሥራ ስንብት |
| 14 | በኮርፖሬሽኑ ንብረት ላይ ዜን ብሎ ጉዳት ማድረስ በማስረጃ ሲረጋገጥ፣ | ከባድ | ለዲስፕሊን ኮሚቴ በማቅረብ የሥራ ስንብት | | | | |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 15 | ማንኛውም የባቡር ትኬት ማጭበርበርን መፈፀም በማስረጃ ሲረጋገጥ | ከባድ | ለዲስፕሊን ኮሚቴ በማቅረብ የሥራ ስንብት | | | | |
| 16 | በተሠጠው የሥራ መዘርዝር መሠረት ሥራ እንዲሠራ ታዞ ያለበቂ ምክንያት በታዘዘውና በሚፈለገው ጊዜ ገደብ ውስጥ ያላከናወነ በማስረጃ ሲደገፍ፣ | ቀላል | የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ በሥራ ክፍሉ በኩል | የ5 ቀን ደመወዝ በሥራ ክፍሉ በኩል | የ15 ቀን ደመወዝ በሥራ ክፍሉ በኩል | የ1ወር ደመወዝ በሥራ ክፍሉ በኩል | ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴቀርቦ እንዲታይ በማድረግ እስከ ሥራ ስንብት |
| 17 | ከተጠየቀው የግዥ መስፈርት (ስፔስፊኬሽን) ውጪ ዕቃ እንዲገዛ ማድረጉ በማስረጃ ሲረጋገጥ፣ | ከባድ | ለዲስፕሊን ኮሚቴ በማቅረብ የሥራ ስንብት | | | | |
| 18 | ገበያ ላይ መገኘት አለመገኘቱን ተገቢውን ጥናት ሳያደርጉ መስፈርት (ስፔስፊኬሽን) በማውጣት ኮርፖሬሽኑን ለተንዛዛ የግዥ ሂደት ማጋለጥ፣ | ከባድ | የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ በስራ ክፍሉ/በአቅርቦትና ንብረት አስተዳደር በኩል | ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ እስከ ሥራ ስንብት | | | |
| 19 | አገልግሎት የማይሰጥን ዕቃ ያለፍላጎት ገዝቶ ማስቀመጥ በማስረጀ ሲረጋገጥ፣ (ማብራሪያ) | ከባድ | ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ እስከ ሥራ ስንብት | | | | |

| ተ.ቁ | የጥፋት አይነት | የጥፋት ደረጃ | የቅጣት እርምጃዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የመጀመሪያ ጥፋት | ሁለተኛ ጥፋት | ሦስተኛ ጥፋት | አራተኛ ጥፋት | አምስተኛ ጥፋት |
| 20 | ያለበቂ ምክንያት ከተፈቀዱ የመጫኛና የማውረጃ ባቡር ጣቢያዎች /ስቴሽኖች/ ውጭ መጫንና ማውረድ በማስረጃ ሲረጋገጥ፣ | ከባድ | ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ እስከ ሥራ ስንብት | | | | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 21 | ኮርፖሬሽኑ ሳያውቀው ወይም ሳያስፈቅድ በኃላፊነት የተሰጠውን ተሽከርካሪ አሳልፎ ለሌላ መስጠት ወይም እንዲነዳ ማድረግ በማስረጃ ሲረጋገጥ፣ | ከባድ | ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ የሥራ ስንብት | | | | |
| 22 | ያለበቂ ምክንያት በተሽከርካሪው ላይ አደጋ ሲደርስበት /ሲያደርስ/ በ24 ሠዓት ውስጥ አስፈላጊውን መረጃ ይዞ ለሚመለከተው ክፍል ያላሳወቀ አሽከርካሪ እንዲሁም የተሽከርካሪ አደጋ መድረሱን አውቆ የኢንሹራንስ አደጋ ቅጽ እንዲሞላ ያላደረገ የኢንሹራንስ ክፍል ሠራተኛ መኖሩ፣ | ከባድ | ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ ከፅሁፍ ማስጠንቀቂያ እስከ ሥራ ስንብት ድረስ | | | | |
| 23 | አንድ አሽከርካሪ የግጭት ጉዳት ደርሶበት ከሌላኛው ወገን የግጭቱን ግምት መቀበሉ፣ | ከባድ | ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ እስከ ሥራ ስንብት | | | | |
| 24 | የሌሉት ፈረቃ ሠራተኛ ሆኖ ያለበቂ ምክንያት **ከ5** ደቂቃ በላይ ያረፈደ፣ | ቀላል | የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ በስራ ክፍሉ | በሥራ ክፍሉ የ5 ቀን ደመወዝ በስራ ክፍሉ | የ15 ቀን ደመወዝ በስራ ክፍሉ | የ1 ወር ደመወዝ ቅጣት በስራ ክፍሉ | ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ እስከ ሥራ ስንብት |

| ተ.ቁ | የጥፋት አይነት | የጥፋቱ ደረጃ | የቅጣት እርምጃዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የመጀመሪያ ጥፋት | ሁለተኛ ጥፋት | ሦስተኛ ጥፋት | አራተኛ ጥፋት | አምስተኛ ጥፋት |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 25 | ከተቀመጠ ፍጥነት በላይ/በታች ባቡር መንዳት፣ ቀይ መብራት ጥሶ ማለፍ በማስረጃ ሲረጋገጥ፤ | ከባድ | በሴፍቲ ማኑዋል መሰረት ተገቢው እርምጃ ይወሰዳል | በሴፍቲ ማኑዋል መሰረት ተገቢው እርምጃ ይወሰዳል | በሴፍቲ ማኑዋል መሰረት ተገቢው እርምጃ ይወሰዳል | በሴፍቲ ማኑዋል መሰረት ተገቢው እርምጃ ይወሰዳል | በሴፍቲ ማኑዋል መሰረት ተገቢው እርምጃ ይወሰዳል |
| 26 | ያለበቂ ምክንያት ወይም የቅርብ ኃላፊው በማያውቀው ሁኔታ በፍ/ቤት ቀጠሮ ላይ ሳይቀርብ በመቅረቱ በኮርፖሬሽኑ መብት እና ጥቅም ላይ ጉዳት ያደረሰ የኮርፖሬሽኑ የሕግ ባለሙያ፤ | ከባድ | እንደ ጉዳዩ ክብደትና ቅለት ታይቶ ከ5 ቀን እስከ 10 ቀን ደመወዝ ቅጣትበሥራ ክፍሉ በኩል | ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ እስከ ሥራ ስንብት | | | |
| 27. | ወደ ዕቃ ግምጃ ቤት የሚገባን ዕቃ በሚመለከተው ባለሙያ ደህንነቱና ጥራቱ ሳይረጋገጥ የተረከበ ባለሙያ ወይም የዕቃ ግምጃ ቤት ሠራተኛ፤ | ከባድ | ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ እስከ ሥራ ስንብት | | | | |
| 28 | አንድን ሠራተኛ ሰብአዊ ክብሩን በሚነካ ሁኔታ የሰደበ፣ የዘለፈ፣ ያዋረደ፣ የደበደበ በማስረጃ ሲረጋገጥ፤ | ከባድ | ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ እስከ ሥራ ስንብት | | | | |
| 29 | በኮርፖሬሽኑ ትዕዛዝ ለሠራተኛው ለሕክምና 100% ከፍሎ ከኤች. አይ.ቪ. በስተቀር ለማስመርመር ሲፈልግ ሠራተኛው አልመረመርም ሲል ፤ | ከባድ | ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ እስከ ሥራ ስንብት | | | | |

| ተ.ቁ | የጥፋት አይነት | | የቅጣት እርምጃዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|

| | | የጥፋት ደረጃ | የመጀመሪያ ጥፋት | ሁለተኛ ጥፋት | ሦስተኛ ጥፋት | አራተኛ ጥፋት | አምስተኛ ጥፋት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 30 | ለደህንነት ሲባል በር ላይ በጥበቃ ሠራተኛ የሚደረገውን ፍተሻ ሲጠየቅ ያልተባበረ ፤ | ከባድ | የመጨረሻ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ በሰው ሃብት ልማት ዘርፍ/መምሪያ/ዲፓርትመንት | ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ እስከ ሥራ ስንብት | | | |
| 31 | ሠራተኛው በቅጥር፣ በዕድገት ሆነ በዝውውር ጊዜ የተሳሳተ መረጃ በመስጠት ኮርፖሬሽኑን ያሳሳተ ወይም ያጭበረበረ መሆኑ በማስረጃ ሲረጋገጥ ፤ | ከባድ | የሥራ ስንብት | | | | |
| 32 | የኮርፖሬሽኑን ወይም ለኮርፖሬሽኑ የቀረበ ማንኛውም ሰነድ ማስረጃ ሆነ ብሎ የቀየረ፣ ያጠፋ፣ የደለዘ ወይም የቀደደ በማስረጃ ሲረጋገጥ፣ | ከባድ | ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ እስከ ሥራ ስንብት | | | | |
| 33 | ለኮርፖሬሽኑ ሆነ ከኮርፖሬሽኑ ጋር የሥራ ግንኙነት ላለው ተቋም ወይም አካል የሐሰት ማስረጃ፣ መረጃ፣ ሰነድ፣ መታወቂያ፣ የምስክር ወረቀት ያቀረበ ወይም ራሱን ወይም 3ኛ ሰው ለመጥቀም ሲል ያሳሳተ ወይም የተሳሳተ መረጃ የሠጠ በማስረጃ ሲረጋገጥ፣ | ከባድ | ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ እስከ ሥራ ስንብት | | | | |
| 34 | የቤተሰቡ አባል ያልሆነን ሰው የነፃ ባቡር መጠቀሚያ መታወቂያ/ትኬት እንዲያገኝ ያደረገ ሠራተኛ | ከባድ | ጉዳዩ ለዲሲፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ እስከ ሥራ ስንብት | | | | |

| ተ.ቁ | የጥፋት አይነት | የቅጣት እርምጃዎች |
|---|---|---|

| | | የጥፋት ደረጃ | የመጀመሪያ ጥፋት | ሁለተኛ ጥፋት | ሦስተኛ ጥፋት | አራተኛ ጥፋት | አምስተኛ ጥፋት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 35 | የኮርፖሬሽኑን ወይም በኮርፖሬሽኑ ኃላፊነት የሚገኝ ንብረት /ጥሬ ገንዘብ ወይም በኮርፖሬሽኑ የሥራ ግንኙነት ምክንያት በሥራ አጋጣሚ ሠራተኛው እጅ ሲገቡ የማይችሉ የደንበኞችን ወይም የሠራተኛን ንብረት /ገንዘብ የሰረቀ፣ የደበቀ፣ ለግል ጥቅም ያዋለ፣ ያሸሸ፣ ያጎደለ ወይም ለሌላ ሰው ያሳለፈ ወይም ለሌላ ሰው እንዲሰረቅ ወይም እንዲወሰድ የተባበረ በማስረጃ ሲረጋገጥ፣ | ከባድ | የሥራ ስንብት | | | | |
| 36 | አግባብ ባለው ባለሥልጣን ፈቃድ ያልተሰጠው ወይም ውስጡ ምን እንደያዘ የማያውቀውን ማንኛውንም እሽግ ወይም ጥቅል በባቡር ለማጓጓዝ የሞከረ ወይም ይዞ የተገኘ ፡ | ከባድ | ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ እስከ ሥራ ስንብት | | | | |
| 37 | ከኮርፖሬሽኑ በሚገኝ ነፃ ትኬት መብት በመጠቀም ሠራተኛውም ሆነ ነፃ ትኬት ተጠቃሚው የሠራተኛው ቤተሰብ ማንኛውንም የሚሄዱበትን ሀገር ሕግ የተላለፈ ፡ | ከባድ | ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ እስከ ሥራ ስንብት | | | | |
| 38 | የውሎ አበል ወስዶ ያለበቂ ምክንያት ሳያሳውቅ በተመደበበት ሥራ ላይ ያልተሰማራ ወይም የተወሰነለትን ሥራ ያልሸፈነ ፡ | ቀላል | የ5 ቀን ደመወዝ ቅጣትና የወሰደውን አበል ተመላሽ ማድረግ | የ15 ቀን ደመወዝ ቅጣትና የወሰደውን አበል ተመላሽ | ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ እስከ ሥራ ስንብት | | |

| ተ.ቁ | የጥፋት አይነት | የጥፋት ደረጃ | የቅጣት እርምጃዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የመጀመሪያ ጥፋት | ሁለተኛ ጥፋት | ሦስተኛ ጥፋት | አራተኛ ጥፋት | አምስተኛ ጥፋት |
| 39 | ሠራተኛው የተሰጠውን ወይም የሚያውቀውን ኮርፖሬሽኑ የሚሰራባቸውን/የተቀበላቸውን የአሰራር ሥርዓቶች በሥራ ላይ አለማዋል፣ አለመከተል በማስረጃ ሲረጋገጥ፣ | ከባድ | የመጨረሻ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ | ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ እስከ ሥራ ስንብት | | | |
| 40 | በምግብ ማደራጃ ክፍል የሚሠራ ማንኛውም የኮርፖሬሽኑ ሠራተኛ የኮርፖሬሽኑን ንፅህና ደንብ ያልተከተለ ፣ | ቀላል | የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ በሥራ ክፍሉ በኩል | የ5 ቀን ደመወዝ በሥራ ክፍሉ በኩል | የ15 ቀን ደመወዝ በሥራ ክፍሉ በኩል | ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ እስከ ሥራ ስንብት | |
| 41 | ለሠራተኛውና ለኮርፖሬሽኑ አሠራርና ደህንነት ሲባል በጽሁፍ የተሰጡ ማስጠንቀቂያዎችን፣ መመሪያዎችንና ስምምነቶችን ወይም ከሥራ ልምድ በግልጽ የሚታወቅ የአሰራር ዘዴን ሥራ ላይ ያላዋለ/ያላከበረ እና ስራ ላይ ያለማዋሉ አደጋ ያስከተለ ወይም ሊያስከትል የሚችል መሆኑ በኮርፖሬሽኑ ሲረጋገጥ | ከባድ | የሥራ ስንብት | | | | |
| 42 | የሥራ አካባቢን በንፅህና ያልያዘ፣ ያቆሸሸ፣ ባልተፈቀደ ቦታ ቆሻሻ የጣለ ፣ | ቀላል | የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ በሥራ ክፍሉ/ሰው ኃብት ልማት መምሪያ/ዘርፍ | የ5 ቀን ደመወዝ በሥራ ክፍሉ/ሰው ኃብት ልማት መምሪያ/ዘርፍ | የ15 ቀን ደመወዝ በሥራ ክፍሉ/ሰው ኃብት ልማት መምሪያ/ዘርፍ | የ1 ወር ደመወዝ ቅጣት በሥራ ክፍሉ/ሰው ኃብት ልማት መምሪያ/ዘርፍ | ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ እስከ ሥራ ስንብት |
| 43 | በኮርፖሬሽኑ በምልክት የተከለከለ ሥፍራ ያለፈቃድ መግባት ፣ | ቀላል | የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ | የ5 ቀን ደመወዝ | የ15 ቀን ደመወዝ | ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ | |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | በማድረግ እስከ ሥራ ስንብት | |

| ተ.ቁ | የጥፋት አይነት | የጥፋት ደረጃ | የቅጣት እርምጃዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | የመጀመሪያ ጥፋት | ሁለተኛ ጥፋት | ሦስተኛ ጥፋት | አራተኛ ጥፋት | አምስተኛ ጥፋት |
| 44 | ከሥራ ጋር በተያያዘ በሠራተኛው ወይም በኮርፖሬሽኑ ንብረት ላይ የደረሰ አደጋን ያላሳወቀ ነገር ግን በቦታው ላይ መኖሩ በማስረጃ ሲረጋገጥ፤ | ቀላል | የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ | የ5 ቀን ደመወዝ | የ15 ቀን ደመወዝ | ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ እስከ ሥራ ስንብት | |
| 45 | የደንበኛን ዕቃ አግባብነት በሌለው መልኩ መያዝ፣ መጫን፣ ማውረድ፣ ማጓጓዝ እና ኮርፖሬሽኑን ለካሣ ክፍያ የሚጋብዘው መሆኑ ፤ | ከባድ | ጉዳዩ ለዲስፕሊን ኮሚቴ ቀርቦ እንዲታይ በማድረግ እስከ ሥራ ስንብት | | | | |
